ባርነት ፡ ቢቀር ፡ የማይፈቅዱ ፡ ሰዎች ፡ ለክርክራቸው ፡ መደገፊያ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ባርያ ፡ ለጌታው ፡ እንዲገዛ ፡ ያዛል ፡ እንጂ ፡ አይከለክልም ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈቀደውን ፡ መሻር ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡ ሲሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተሰምተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ መልካምና ፡ ክፉን ፡ የሚለይበት ፡ ዕውቀት ፡ የሰጠው ፡ እድሉን ፡ እያሻሻለ ፡ እንዲሄድ ፡ ነው ። ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ መልካምን ፡ እንጂ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልፈቀደለትም ። ደካማነቱን ፡ እያየ ፡ የሚያሳልፍለት ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ቢኖርም ፡ ሰው ፡ ጥቅሙንና ፡ ጉዳቱን ፡ እያመዛዘነ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ከክፉ ፡ ለመራቅ ፡ በመጣጣር ፡ ፈንታ ፡ በስሕተቱ ፡ ጸንቶ ፡ ዘለዓለም ፡ ሊኖር ፡ ማሰብ ፡ አይገባውም ። ለምሳሌ ፡ በጦርነት ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ መጋደል ፡ እግዚአብሔር ፡ አልከለከለም ተብሎ ፡ ሰው ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ የጦርነትን ፡ ጉዳት ፡ እንዲመሸሽና ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ እንደማስወገድ ፡ ሁሉ ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ አድርጎት ፡ ሊኖር ፡ ይገባዋልን ? ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሰበብ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

በዓለም ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ባሮች ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ይቆጠሩ ፡ በነበሩበት ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ቅዱስ ፡ አውጉስጢኖስ ፡ ሲናገር ፤

«እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ አድርጎ ፡ በራሱ ፡
«አምሳል ፡ ሲፈጥረው ፡ ዕውቀት ፡ የሌላቸውን ፡ ፍጡሮች ፡
«እንዲገዛቸው ፡ ፈቀደ ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ሰው ፡ ባርያ ፡
«አድርጎ ፡ እንዲገዛው ፡ አላዘዘም ፡ » ብሏል ።

ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ከፈለገ ፡ ዕውቀት ፡ አያንሰውም ፡ ትልቅ ፡ ጭንቅ ፡ የሚሆንበት ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ የሚጠላበትን ፡ ነገር ፡ ለበጎ ፡ ምግባር ፡ ሲል ፡ ጥቅሙን ፡ ንቆ ፡ ለመፈጸም ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ካሰብንማ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ቢያደርጉብህ ፡ የማትወደውን ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አታድርግ ፡ ብሎ ፡ ጨርሶት ፡ የለምን ? የባርነት ፡ ቀንበር ፡ ቢወድቅበት ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ ይገኛልን ? ብለው ፡ የባርነት ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ሲመልሱላቸው ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡



ለክርክራቸው ፡ መሠረት ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስቡት ፡ ሰዎች ፡ የሚመልሱት ፡ አያገኙም ።

ሰው ፡ ከዘመን ፡ ወደ ፡ ዘመን ፡ በመተላለፍ ፡ እውቀቱ ፡ እየዳበረ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ሲደርስ ፡ በልማድ ፡ መጋረጃ ፡ ተሸፍነው ፡ ከሚኖሩት ፡ ስሕተቶች ፡ አንዱ ፡ የባርነት ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ በቶሎ ፡ ሊረዳው ፡ ዘንድ ፡ የማይቀር ፡ ነገር ፡ ነበር ። እነሆ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የባርነት ፡ መወገድ ፡ መጀመሪያ ፡ ከተፈጸሙት ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራዎች ፡ አንደኛው ፡ ሆነ ። የአእምሮ ፡ ዓይናቸው ፡ የራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ከሆነው ፡ ነገር ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ከፍተኛ ፡ የሕሊና ፡ ጉዳይ ፡ የማይመለከትላቸው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ባርነትን ፡ የሚፈቅድ ፡ አስመስለው ፡ ቢተረጉሙት ፡ እውነተኛው ፡ የታሪክ ፡ ማስረጃ ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ልብ ፡ የጠባይ ፡ አልማዝ ፡ የሆነውን ፡ የርኅራኄ ፡ የፍቅርና ፡ የመተዛዘንን ፡ ስሜት ፡ በመፍጠሩ ፡ የባርነት ፡ ግፍ ፡ ከለም ፡ ላይ ፡ እንዲወገድ ፡ ለማድረግ ፡ ዋና ፡ የረዳ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ እንደሆነ ፡ በግልጥ ፡ ይመሰክራል ።

በፍልስፍና ፡ ክንፍ ፡ የሰው ፡ መንፈስ ፡ ሊደርስበት ፡ ከሚችለው ፡ ከመጨረሻው ፡ ያሳብ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የደረሱት ፡ ከጥንቱ ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፎች ፡ ዋና ፡ ዋኖቹ ፡ እንደነ ፡ ፕላቶንና ፡ አርስጣጣሊስን ፡ የመሰሉት ፡ ያልመረመሩትና ፡ ያላጠኑት ፡ ያለም ፡ ጉዳይ ፡ ስለሌለ ፡ የባርነትንም ፡ ጉዳይ ፡ በሰፊው ፡ ተከራክረውበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ ከነዚሁም ፡ ከላይ ፡ የጠራናቸው ፡ ሁለቱ ፡ ፈላስፎች ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ አጸደቁት ፡ እንጂ ፡ ነውርነቱ ፡ አልታያቸውም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ በማድረጋቸው ፡ አይፈረድባቸውም ። የሰይጣን ፡ ተንኰል ፡ የሆኑት ፡ ቊጥራቸው ፡ የበዛ ፡ አማልክቶቻቸው ፡ እነ ፡ ጁፒተርና ፡ አጶሎን ፡ ሌሎቹም ፡ ሁሉ ፡ አሳብ ፡ የሚያበክን ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ የሆነ ፡ ተረታዊ ፡ ጨዋታ ፡ ሲፈጥሩላቸው ፡ መንፈስን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ የሚያውል ፡ እንደ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ፍቅርና ፡ ርኅራኄን ፡ የሚያስተምር ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ያለ ፡ ጠቃሚ ፡

የሆን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ሕጋዊ ፡ ትምህርት ፡ አላስተማሩዋቸ ውም ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ፍቅር ፡ ከሌለ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ እንዳለው ፡ የግሪክ ፡ ፈላስፎች ፡ በዚያ ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ፍቅር ፡ ስላላስተማራቸው ፡ ለዚህ ፡ ትልቅ ፡ ጉዳይ ፡ የሚገባውን ፡ አስተያየት ፡ ሊሰጡት ፡ አልቻሉም ። መንፈሳቸው ፡ በክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ የተቃኘ ፡ ሊቃውንት ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የተሸፈነበትን ፡ የልማድ ፡ መጋረጃ ፡ ቀደደው ፡ የባርነትን ፡ ነውር ፡ በሕሊና ፡ አደባባይ ፡ እርቃን ፡ ሥጋውን ፡ ገልጠው ፡ ለዓ ለም ፡ አሳዩ ። ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ «የአንክል ፡ ቶም ፡ ጐጆ ፡» በሚል ፡ ስያሜ ፡ ባርነትን ፡ ተቃዋሚ ፡ ከሆነች ፡ ከንዲት ፡ ያሜሪካ ሴት ፡ የተጻፈው ፡ ደራሲዋን ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ ያመሰገነበት ፡ መጽ ሐፍ ፡ ባርነትን ፡ ለማስወገድ ፡ የክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደረዳ ፡ የበቃ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ባለቤቱ ፡ ያረከሰውን ፡ አሞሌ ፡ ባለዕዳ ፡ አይከፈለውም ፡ እንደ ሚባለው ፡ ተረት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ በአርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የተፈ ጠረውን ፡ የተቀደሰ ፡ ፍጡር ፡ ባርያ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ከብትና ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ሲሸጠውና ፡ ሲለውጠው ፡ በአእምሮ ፡ አስተያየት ፡ ውርደቱን ፡ ተካፋይ ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ ትልቅ ፡ ዕውቀት ፡ የሚያሻ ፡ አይደለም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባርነት ፡ እንዲቀር ፡ ሥልጣኔና ፡ አእምሮ ፡ የሚያዙት ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ሰዎች ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ የመፈጸሙ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያዳግት ፡ ጭንቅ ፡ ሆኖባቸው ፡ ሲኖር ፡ አብነቱ ፡ በምን ፡ አኳሆን ፡ እንደ፡ተሰጠ ፡ ያፈጸጸሙ ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ ሊያስታውሱት ፡ የሚገባ ፡ ነው ።

ሰው ፡ በሕሊናው ፡ ክፉና ፡ ደጉን ፡ እያመዛዘነ ፡ ከማስተዋሉ ፡ የተነሣ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቀለሙ ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ጥቁር ፡ ወይም ፡ ብጫ ፡ ቢሆን ፡ ፍጡርነቱ ፡ ሁሉም ፡ እኩል ፡ ስለሆነና ፡ ሁሉም ፡ የክብር ፡ ስሜት ፡ ስላለው ፡ ይህ ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ያገኘው ፡ ሰብ አዊ ፡ መብቱ ፡ በሌሎቹ ፡ ዘንድ ፡ የሚገባውን ፡ አስተያየት ፡ ሊያ ገኝ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ የተረ ዱበት ፡ ዘመን ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዓለም ፡



የሚታወቅበትና ፡ የሚበጠበጥበት ፡ ጉዳይ ፡ በሳብና ፡ በትምህርት ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ የሚኖር ፡ እንጂ ፡ በሥራና ፡ በአድርጎት ፡ ሊፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ እየታየ ፡ ሲኖር ፡ የፈረ ንሣዊ ፡ ሬቮሊሲዮን ፡ የተፈጸሚነቱን ፡ ብሥራት ፡ ለዓለም ፡ ያሰማ ፡ መለከት ፡ ሆነ ።

የፈረንሣዊ ፡ ሬቮሊሲዮን ፡ ባርነትን ፡ ከስወገደ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ብቻ፡ የማይበቃ ፡ መስሎ ፡ ስለታየው ፡ በሰንት ፡ ዶሚንግ ፡ ቅኝ ፡ አገሩ ፡ የሚኖ ሩት ፡ ሻንቅሎች ፡ ወኪሎቻቸውን ፡ እንዲልኩ ፡ አድርጎ ፡ በኮንቨንሲዮን፡ መንግሥት ፡ ጉባዔ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ተደረገላቸው ።

የካቲት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፯፻፺፬ ፡ ዓ. ም. የጥቍሮቹ ፡ ሕዝብ ፡ ዋና ፡ መልክተኛ ፡ ከሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ጉባዔ ፡ ዘንድ ፡ ቀርቦ ፡ የወ ንድማማችነትን ፡ መንፈስ ፡ ለመግለጥና ፡ በጥቍሮችና ፡ በነጮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነትም ፡ የተደመሰሰ ፡ መሆኑን ፡ በጉልህ ፡ አብ ነት ፡ ለማስረዳት ፡ ሲል ፡ የኮንቨሲዮን ፡ ፕሬዚዳን ፡ ተነሥቶ ፡ የጥቍ ሩን ፡ መልክተኛ ፡ በሳመው ፡ ጊዜ ፡ የደስታና ፡ የመደነቅ ፡ መንፈስ ፡ ጉባዔውን ፡ አናወጠው ።

በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ሮቤስፒዬር ፡ በአፈ ፡ ጉባዔ ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ክቡር ፡ ፕሬዚዳን ፡ ሆይ ፡ « በጉባዔው ፡ አዳራሽ ፡ በመጀ መሪያው ፡ ግንባር ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ የተቀመጠች ፡ የጥቁር ፡ ተወ ላጅ ፡ የሆነች ፡ አንዲት ፡ አሮጊት ፡ ይህን ፡ የተፈጸመውን ፡ ነገር ፡ አይታ ፡ ከደስታዋ ፡ ስሜት ፡ የተነሣ ፡ አዘርዋት ፡ ከመቀመጫዋ ፡ ላይ ፡ ወደቀች ። ይህ ፡ ነገር ፡ ሳይረሳ ፡ በታሪክ ፡ የዘላለም ፡ ይሕ ወት ፡ አግኝቶ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ በፕሮቶኮል ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ እንዲጽፉት ፡ የጉባዔውን ፡ ጸሓፊዎች ፡ እንዲያዚቸው ፡ አሳስባለሁ » ብሎ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ ።

ሮቤስፒየር ፡ በተናገረው ፡ በዚህ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ነገሩ ፡ በመዝገብ ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ ፕሬዚዳኑ ፡ ተነሥቶ ፡ «በፈረን ሣዊ ፡ ሬቮሊሲዮን ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ በመላው ፡ የፈረንሣዊ ፡ ግዛቶችና ፡ በቅኝ ፡ አገሮቿም ፡ ሁሉ ፡ ባርነት ፡ ለዘላለም ፡ የተወገደ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቃለሁ ፡» ብሎ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ በጉባዔውና ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆኖ ፡ ተጨበጨበ ።

ተያየት ፡ ወደ ፡ ዴሞክራሲ ፡ መንፈስ ፡ ሲያደላ ፡ የደቡብ ፡ ወገኖች ፡ ዋና ፡ ሥራቸው ፡ አትክልት ፡ የሆነው ፡ አሳባቸው ፡ ወደ ፡ « አሪስቶ ክራሲ ፡ » ያደላል ።

ዋና ፡ የአሳብ ፡ መለያየትን ፡ በመካከላቸው ፡ የፈጠረባቸው ፡ የባርነት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። የሰሜን ፡ ወገኖች ፡ ባርነትን ፡ ማስወገድ ፡ ሲሹ ፡ በደቡብ ፡ ያሉት ፡ የአገሩ ፡ አየር ፡ ሞቃት ፡ ከመሆኑ ፡ የተ ነሣ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ላውሮፓውያን ፡ ሰዎች ፡ ያልተመቸ ፡ በመ ሆኑ ፡ ባሮቻቸውን ፡ ነፃ ፡ ለመልቀቅ ፡ አልወደዱም ።

ሊንኮልን ፡ ባርነትን ፡ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ ነበር ። ኒው ፡ አርሊ ያን ፡ በምትባለው ፡ ከተማ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሊንኮልን ፡ በልጅነቱ ፡ ሰዎች በሐራጅ ፡ ባርያ ፡ ሲሸጡ ፡ አይቶ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ አዘነ ። ይህ ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ በመንፈሱ ፡ ብርቱ ፡ የሆነ ፡ የተቃዋሚነት ፡ አሳብ ፡ ስላሳደረበት ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ባርያ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድ ረግ ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ ከመታገል ፡ አላቋረጠም ። ከድህነት ፡ ተነ ሥቶ ፡ በድካሙና ፡ በገልግሎቱ ፡ ማዕርግ ፡ እየጨመረ ፡ ሔዶ ፡ የተ ባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለመሆን ፡ እስከ ፡ ደረሰ ፡ ድረስ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ በመንግሥቱ ፡ መማክርት ፡ ጉባዔ ፡ ላይ ፡ ሊንኮልን ፡ በተናገራቸው ፡ ቀኖች ፡ ዲስኩሮች ፡ ሁሉ ፡ የባርነትን ፡ ሥራ ፤ ከመቃወምና ፡ ከመንቀፍ ፡ አልቦዘነም ። «ነፃ ፡ በሆኑ ፡ አዲሶች ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ድሆች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሕይወታቸውን ፡ የሚያሻሽሉበት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡» እንጂ ፡ ባርያ ፡ ሆነው ፡ ሊገዙበት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፡ ይል ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ የሊንኮልን ፡ ቃሎች ፡ በታሪክ ፡ ሲጠቀሱ ፡ የሚኖሩና ፡ የማይረሱ ፡ ናቸው ። «በውስጧ ፡ እርስ ፡ በርሷ ፡ የተከፋ ፈለች ፡ ንብረት ፡ ዕድሜ ፡ የላትም ። ስለዚህ ፡ ግማሹ ፡ ነፃ ፡ ግማሹ ፡ ባርያ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ የእኛ ፡ መንግሥት ፡ የሚዘ ልቅ ፡ አይመስለኝም ።»

የባርነት ፡ ጉዳይ ፡ ሥር ፡ በሰደደበት ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ሊንከ ልን ፡ የተከተለው ፡ ይህ ፡ አሳብ ፡ ያለፈውን፡ስሕተት ፡ በማረም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ዓለም ፡ ለሚመኘው ፡ የሥልጣኔ ፡ ዘመን መልካም ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ የአዲሱ ፡ ትውልድ ፡ መንፈስ ፡ ስለነፃነት



አሳብ ፡ ወደሚዘጋጅበት ፡ መንገድ ፡ የሚመራው ፡ መሆኑን ፡ በመገን ዘብ ፡ በሰሜን ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ደጋፊዎችና ፡ ረዳቶች ፡ ሲያገኝ ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ተቀዋሚዎች ፡ ተነሡበት ።

ባርነት ፡ እንዲቀር ፡ የሚፈቅዱት ፡ አብዛኞቹ ፡ በመሆናቸው ፡ ሊንኮልን ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ፕሬዚዳንትነት ፡ ተመርጦ ፡ ስለተሾመ ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ በባርያ ፡ ንግድና ፡ በባርያ ፡ ድካም ፡ የሚያገኙትን ፡ ጥቅም ፡ መተው ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ጉዳት ፡ መስሎ ፡ ታይቷቸው ፡ የደቡብ ፡ አሜሪካና ፡ የሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ እንዲለያዩ ፡ አደረጉ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የደ ቡብ ፡ ካሮሊን ፤ ሚሲሲፒ ፤ ፍሎሪድ ፡ አላባማ ፤ ጂዎርጊ ፤ የሚ ባሉት ፡ አገሮች ፡ ካንድነታቸው ፡ ኮንፌዴራሲዮን ፡ ወጡ ። ይህም ፡ አሳብ ፡ በአሜሪካኖች ፡ መካከል ፡ ጠብን ፡ ፈጥሮ ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነትን ፡ አስነሣ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፡ ያለበትን ፡ ኃላፊነት ፡ ዘንግ ተው ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ በማሰብ ፡ ወንድማማች ፡ በሆነ ፡ በአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ውስጥ ፡ ጦርነት ፡ እስከ ፡ መፍጠር ፡ ቢደርሱ ፡ ሊንኮልን ፡ መንፈሱ ፡ የሚወላውል ፡ ሰው ፡ ስላልነበረ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈሰውን ፡ ደም ፡ ለማስቀረት ፡ ሲል ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ የተከተለውን ፡ አሳብ ፡ ለመሻር ፡ ሳይቃጣ ፡ ነገሩን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፋበት ።

በ፲፰፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ጦርነቱ ፡ ተጀመረ ። በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የሰሜን ፡ ጦር ፡ መሪዎች ፡ የሆኑት ፡ ተሸነፉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሁለ ተኛው ፡ ዓመት ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፤ የሰሜን ፡ ወገኖች ፡ በረቱ ። በ፲፰ ፻፷፫ ፡ ዓ. ም. የሰሜን ፡ አሜሪካ ፡ ድል ፡ አድራጊነቱ ፡ ተረጋገጠ ። በ፲፰፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ለባርነት ፡ ተቃዋሚነት ፡ መንፈስ ፡ መሪ ፡ የሆ ነው ፡ ሊንኮልን ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ፕሬዚዳን ፡ ሆኖ ፤ ተመረጠ ። እሱም ፡ በደቡብ ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ሙሉ ፡ እንዲሆንና ፡ የባርነት ፡ ጉዳይ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ዋና ፡ አሳቡ ፡ መሆኑን ፡ ስለገለጠ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ በደቡብ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የድል ፡ አድራጊነቱን ፡ ሥራ ፡ በሙሉ ፡ ፈጸመ ። ሊንኮልን ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ አሳቡን ፡ ከፍጻሜ ፡ ካደረሰና ፡

ኢጣሊያ ፡ በየጋዜጣውና ፡ ለፕሮፓጋንዳ ፡ በምታሳትማቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ባርነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እንዲጠፋ ፡ ያደረገች ፡ ኢጣሊያ ፡ ናት ፡ እያለች ፡ ኢትዮጵያን ፡ በያዘችበት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ትፎክር ፡ ነበር ።

የዚህ ፡ አነጋገርዋ ፡ ትርጕሙ ፡ ባሪያ ፡ ባገራችሁ ፡ ስላላጠፋችሁ፡ ባሮች ፡ ላደርጋችሁ ፡ ዘንድ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያህል፡ ነው ። ይህም ፡ ሮማ ፡ ካርታጐን ፡ ባጠፋች ፡ ጊዜ ፡ የተደረገውን ፡ ፍርድ ፡ የመሰለ ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ሮማዊ ፡ ፍርድ ፡ ነው ። ኢጣሊያም ፡ ሆነች ፡ ማንኛውም ፡ ወቃሽ ፡ የሆነ ፡ መንግሥት ፡ ይግባቸው ፡ ተሰሚ ፡ የሚሆነው ፡ ኃይለኞች ፡ በመሆናቸው ፡ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ ነገር ፡ ተከራካሪዎች ፡ ሆነው ፡ አለመሆኑን ፡ ታሪክ ፡ ይመሰክራል ። በላይኛው ፡ ክፍል ፡ እንዳመለከትነው ፡ የቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ ያገኙትው ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ገጥሟታል ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በጎ ፡ አሳቧን ፡ የገለጸችውማ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ነው ።



## ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ጕዳዩ ፡ ስላለመፈጸሙ ።

የባርያ ፡ ንግድ ፡እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ በአፄ ፡ ዮሐንስና ፡ በእንግሊዝ ፡ንግሥት ፡ ቪክቶሪያ ፡ መካከል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ውል ፡ ተፈርሟል ።

ግርማዊት ፡ የታላቋ ፡ ብሪታንያና ፡ የዩናትድ ፡ ኪንግደምና ፡ የአየርላንድ ፡ ንግሥት ፤ የሕንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ እንዲከለከልና ፡ ጨርሶም ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ አስበው ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ስለፈቀዱ ፡ ይኸው ፡ ውል ፡ በራሳቸውና ፡ በወራሾቻቸው ፡ ላይ ፡ ይጸናል ። ለዚሁም ፡ በምሥራቅ ፡ የሕንድ ፡ አገር ፡ የግርማዊት ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ አዛዥ ፡ የሆኑት ፡ ሪየር ፡ አድሚራል ፡ ሰር ፡ ዊሊያም ፡ ሑዊት ፡ በግርማዊት ፡ የታላቋ ፡ ብሪታንያና ፡ የአየርላንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥት ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ሆነው ፡ ከዚህ ፡ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ አንቀጾች ፡ ተስማምተው ፡ ተዋውለዋል ።

### አንደኛ ፡ አንቀጽ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ ባርያ ፡ እንዳይገዛና ፡ እንዳይሸጥ ፡ በተቻላቸው ፡ መጠን ፡ ሊከለክሉና ፡ እንዲቀር ፡ ሊያደርጉ ፡ ተስማምተዋል ።

### ሁለተኛ ፡ አንቀጽ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ባርያ ፡ ከውጭ ፡ እየተገዛ ፡ ወደግዛታቸው ፡ እንዳይገባ ፡ ወይም ፡ ካገራቸው ፡ እየተሸጠ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንዳይወጣ ፡ ባላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሊያስከለክሉና ፡ ሊያስወግዱ ፡ ተስማምተዋል ።

## ሦስተኛ ፡ አንቀጽ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በላቸው ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ነፃ ፡ የወጡትን ፡ ባሮች ፡ ሊጠብቋቸው ፡ ሊበድላቸው ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ከባርነት ፡ ሊመልሳቸው ፡ የሚሞክር ፡ ሰውም ፡ ቢገኝ ፡ በብርቱ ፡ እንዲቀጣ ፡ ሊያደርጉ ፡ ውል ፡ ገብተዋል ።

## አራተኛ ፡ አንቀጽ ።

ግርማዊት ፡ የብሪታንያ ፡ ንግሥት ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ባሮች ፡ እያሣፈሩ ፡ የሚያዘዋውሩትን ፡ የማናቸውንም ፡ የሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ የሆኑትን ፡ መርከቦች ፡ የግርማዊት ፡ የመርከብ ፡ ሹማምንቶች ፡ እንዲይዟቸው ፡ የሚፈቅዱላቸው ፡ ውሎች ፡ ስላሏቸው ፡ የግርማዊት ፡ የመርከብ ፡ ሹማምንቶች ፡ በሚይዟቸው ፡ መርከቦች ፡ ላይ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዜጎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በባርነት ፡ ስም ፡ ተይዘው ፡ ቢገኙ ፡ ነፃ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ሊያደርጉና ፡ እነዚህንም ፡ ዜጎች ፡ ወደ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ እንዲመለሱ ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ሊፈጽሙ ፡ ውል ፡ ገብተዋል ።

## አምስተኛ ፡ አንቀጽ ።

ይህ ፡ ውል ፡ እንዲጸድቅ ፡ ይደረጋል ። ከጸደቀችም ፡ በኋላ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ አድዋ ፡ ተመልሶ ፡ ይላካል ።

ለዚሁ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሬየር ፡ አድሚራል ፡ ሰር ፡ ዊሊያም ፡ ሂዊት ፡ በታላቋ ፡ ብሪታንያና ፡ በአይርላንድ ፡ ንግሥት ፡ በሕንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥት ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ፈር መውበታል ፡ ወይም ፡ ማኅተማቸውን ፡ አትመውበታል ። ተጻፈ ፡ በአ



ድዋ ፡ ሰኔ ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፺፮ ፡ ዓ. ም. (እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ) ግንቦት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ. ም. (እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ። )

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ማኅተም

ፊርማ ፡ ዊሊያም ፡ ሒዊት ።

ይኸው ፡ ውል ፡ ከግርማዊት ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ቀርቦ ፡ ከጸደቀች ፡ በኋላ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፺፮ ፡ ዓ. ም. የጸና ፡ ሆኗል ።

አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ይህን ፡ ውል ፡ ሲፈራረሙ ፡ ባርነትን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ለማስወገድ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ እንደነበራቸውና ፡ ባሳባቸው ፡ እንደቆረጡ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ ስላልፈቀደላቸው ፡ ሊፈጽሙት ፡ አልቻሉም ። ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ እንደ ምንመለከተው ፡ አፄ ፡ ምኒልክም ፡ አሰቡት ፡ እንጂ ፡ አልሆነላቸውም ።

ባርነትን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ለማጥፋት ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ ስላልፈቀደላቸው ፡ አልቻሉም ። ኋላም ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ቀጥሎም ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ባርነትን ፡ ለማስወገድ ፡ አስበውበት ፡ ነበር ። አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሥልጣኔ ፡ ብርሃን ፡ ወደ ፡ አገርዋ ፡ እንዲገባ ፡ ሙሉ ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኗንና ፡ ስለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጉዳይ ፡ የቀረቡት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ የሚስማሙበትን ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ለመከፈል ፡ መመኘቷዋን ፡ እየገለጹ ፡ በንድ ፡ ዓይነት ፡ ቃል ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ለአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ሲልኩ ፡ በፍቼ ፡ ከተማ ፡ ሆነው ፡ ኅዳር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ. ም. (እ. አ. አ.) ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ በላኩት ፡ ደብዳቤ ፡ ውስጥ ፡ ስለባርያ ፡ ጉዳይ ፡ የጻፉት ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

«ባርነትን ፡ ለማጥፋት ፡ ክርስቲያኖች ፡ በሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ስለሰማሁና ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ነፃነት ፡ ከሚሠራው ፡ ከዚህ ፡ ስምምነት ፡ ለመለየት ፡ ስላልፈቀድሁ ፡ በጋሎች ፡ ላይ ፡ ባደረግሁት ፡ ዘመቻ ፡ በየጊዜው ፡ ወታደ

ሮቹ ፡ እየማረኩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሃያ ሺህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ባሮች ፡ ሲያመጡ ፡ ነፃነት ፡ እየሰጠሁ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ እንዲገቡ ፡ አድርጌአለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ ማዶ ፡ ያሉት ፡ ሕዝቦች ፡ በገሬና ፡ በጋሎችም ፡ አገር ፡ እየገቡ ፡ ልጆች ፡ ሰርቀው ፡ እየወሰዱ ፡ በዓረብ ፡ አገርና ፡ በየባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ከመሸጥ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የላቸውም ። »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፹፩ ፡ ዓ. ም. ዱብረ ፡ ብርሃን ፡ ሳሉ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ በጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ውስጥ ፡ ስለባርያ ፡ ጉዳይ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይገኝበታል ።

« እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ጀምሬአለሁ ፡ ይኸውም ፡ በክፉ ፡ በኩል ፡ የሚመጣውን ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ እንዲወገድ ፡ ማድረጌ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ የባርያ ፡ ነጋዴዎች ፡ ባገሬ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይተላለፉ ፡ ከልክያለሁ ። »

ቆይቶ ፡ ደግሞ ፡ ግንቦት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፹፱ ፡ ዓ. ም. አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ በተዋዋሉት ፡ የውጫሌ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በአሥራ ፡ አራተኛው ፡ አንቀጽ ፡ የባርያን ፡ ንግድ ፡ ከገራቸው ፡ ሊያስወግዱና ፡ በግዛታቸውም ፡ ውስጥ ፡ የባርያ ፡ ነጋዴዎች ፡ እንዳይተላለፉ ፡ ሊከለክሉ ፡ ተዋውለዋል ። ደግሞ ፡ ባርነትን ፡ ለማጥፋት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በብሩክሴል ፡ ከተማ ፡ ባደረጉት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ አብረው ፡ ተስማምተዋል ።



ባርነት ፡ ባፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ መወገዱ ።

ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በልማድ ፡ ሰንሰለት ፡ ከትውድል ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ እየተላለፈ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣውን ፡ ባርያ ፡ የመግዛትን ፡ ልማድ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ብርቱ ፡ የሆነ ፡ አዋጅ ፡ በማወጅና ፡ በቁርጠኛ ፡ አሳብ በመሥራት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ያገ ፡ ለቀቅ ፡ በማድረግ ፡ የማይፈጸም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ሆኑ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በወረቀት ፡ ተዋዋሉበት ፡ እንጂ ፡ ከፍጻሜ ፡ ሊያደርሱት ፡ ስላልቻሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊንከልን ፡ የሆኑት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እስከነሡ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ሊፈጸም ፡ አልቻለም ። የባርያ ፡ ነፃ ፡ ዳኛ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማና ፡ በያውራጃው ፡ ቆሞ ፡ የፈቀደ ፡ ባርያ ፡ ሁሉ ፡ ነፃነቱን ፡ በዳኛ ፡ ፊት ፡ እያረጋገጠ ፡ ነፃ ፡ እንዲወጣ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ የሚያገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ባለማስተዋልና ፡ ከዚህም ፡ የበለጠ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ በመፈጸሟ ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ የምታገኘውን ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ባለመገንዘብ ፡ ርስቱን ፡ እንደተነቀለ ፡ ያህል ፡ ቅያሜ ፡ ገብቶት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሁላችንም ፡ እናስታውሰዋለን ።

በቀሩት ፡ አገሮች ፡ የተደረገውን ፡ ስንመለከተው ፡ ሕዝቡም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ በማድረጉ ፡ አይፈረድበትም ፡ በኤኮኖሚም ፡ ሆነ ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ ይህንን ፡ ጥቅሙን ፡ ስለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ለማድረግ ፡ የተዘጋጀ ፡ አልነበረም ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አስቸጋሪ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ አሳቡን ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትጋትና ፡ ያሳብ ፡ ጽኑነት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። በየጊዜው ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ከወጡት ፡ አዋጆች ፡ ለምሳሌ ያህል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ አንዱን ፡ እንጠቅሳለን ።

የተሾሙ ፡ ዳኞች ፡ እያስቆጠሩ ፡ በየስማቸውም ፡ በመዝገብ ፡ እያስ ጻፉ ፡ በጌቶቻቸው ፡ ቤት ፡ እንዲኖሩ ፡ ያደርጉዋቸዋል ። ከውስጣቸ ውም ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕለቱን ፡ ለዳኛ ፡ አስታውቀው ፡ መሞቱን ፡ በመዝገብ ፡ ያጽፉ ። መሞቱን ፡ ለዳኛ ፡ ሳያስታውቁና ፡ አመዝገብ ፡ ሳያስጥፉ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ በባሪያ ፡ ፈንጋይ ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣሉ ፡ በሚለው ፡ ላይ ፡ ባሮች ፡ በመሸጥ ፡ በየሚጠረ ጠሩ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ ሕፃና ቱም ፡ በሙሉ ፡ ተቆጥረው ፡ በመዝገብ ፡ እንዲጻፉ ፡ ከተጻፉም ፡ በኋላ ፡ ያውራጃው ፡ ሹምና ፡ ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ለዚሁም ፡ በተለየ ፡ የታ ዘዘው ፡ ቆጣሪ ፡ በመዝገቡ ፡ እየፈረመ ፡ ለዋናው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ እንዲያስረክቡ ፡ አገረ ፡ ገዥውም ፡ አንድ ፡ ግልባጭ ፡ በትልቁ ፡ አውራጃ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አስቀርቶ ፡ ዋናውን ፡ መዝገብ ፡ ላገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲልክ ። ከተቆጠረና ፡ በመዝገብም ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ባምስት ፡ ባምስት ፡ ዓመት ፡ እንደገና ፡ እየተቆጠረ ፡ የተወ ለደውና ፡ የሞተው ፡ እንዲታወቅ ፡ እንደፈተኛው ፡ የተቆጠረበት ፡ መዝገቡ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲላክ ፡ ደንብ ፡ ተደ ርጓል ፡ ተብሎ ፡ ታድስዋል ።

አራተኛ ።

ወደፊት ፡ ባርነት ፡ በጭራሽ ፡ እስከሚጠፋበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ባሮች ፡ ነፃነት ፡ የሚያገኙበት ፡ ደንብ ፡ እየታየ ፡ እንዲሻሻልና ፡ እን ዲታደስ ፡ ተፈቅዷል ።

ሐምሌ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ምሕረት ።



ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አዋጅ ፡ ማውጣት ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፡ እምቢተኛ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ አዋጁን ፡ መፈጸም ፡ ደግሞ ፡ ለብቻው ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ባርነትን ፡ እንዲ ያጠፉ ፡ ሲያስቸግሩዋቸው ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሕዝቡ ፡ በማ ነኛውም ፡ ረገድ ፡ ያልተዘጋጀ ፡ በመሆኑ ፡ አዋጁን ፡ አልፈጸምም ፡ ብሎ ፡ ስላወከቻቸው ፡ ያወጡት ፡ አዋጅ ፡ ቃል ፡ ይህን ፡ ያሉበትን ፡ አስቸጋሪ ፡ ሁኔታ ፡ በትክክል ፡ ይገልጣል ። ቃሉም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

« የባርያ ፡ ነገር ፡ አትሽጥ ፡ አትግዛ ፡ ብዬ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡
« ባዋጅ ፡ አስከልክዬ ፡ ነበር ። አንተ ፡ ግን ፡ ውስጥ ፡ ለው
« ስጥ ፡ መሸጥክን ፡ መግዛትህን ፡ የማትተው ፡ ሆንክ ። ይል
« ቁንም ፡ በዳር ፡ በዳር ፡ ያለው ፡ ሚስቱንም ፡ ልጁንም ፡
« ይሸጥ ፡ ጀመር ፡ ማለት ፡ ሰማሁ ። አሁንም ፡ በዳር ፡ አገ
« ርም ፡ በሌላም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ባርያ ፡ መሸጥና ፡ መግ
« ዛትክን ፡ ተውኝ ። እንግዴህ ፡ ግን ፡ ባርያ ፡ ስትሸጥ ፡ ስት
« ገዛ ፡ የተገኘህ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ዘመድህ ፡ እያሰርኩ ፡ ሥራ ፡
« ለሚያሠራ ፡ ሰው ፡ እሰጥሃለሁ ።

አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ለማስፈራራት ፡ ያህል ፡ ይህን ፡ ተናገሩ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ አዋጅ ፡ ለማስፈጸም ፡ እንዳልቻሉ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ።

አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ አሳቡን ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ አዋጁን ፡ በሥራ ፡ መፈጸም ፡ መሆኑን ፡ አስተው ለው ፡ እንዴት ፡ እንደሠሩ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ እንሰጣለን ።

በኢትዮጵያ ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ባለ ፉት ፡ አርእስቶች ፡ እንደተመለከትነው ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ የግብር ፡ ጓደኞቻቸው ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ያህል ፡ ሳይሆን ፡ ይህን ፡ ዐመፀኛ ፡ ሥራቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ አንዳንድ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ከመሥራት ፡ አልተመለሱም ።

ይልቁንም ፡ መንግሥት ፡ በጠበቀ ፡ አዋጅ ፡ ካስከለከለ ፡ በኋላ ፡ ባርያ ፡ ፈንጋዮች ፡ ብዙ ፡ ባሮች ፡ ይዘው ፡ ለመሸጥ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡

አንዱ ፡ አገር ፡ ሲዘዋወሩ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚሄዱት ፡ ሌሊት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንዳይያዙ ፡ ሁልጊዜ ፡ በፍጥነት ፡ መገሥገሥ ፡ ነበረባቸው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ባሮቹ ፡ ሲደክሙባቸው ፡ እንዳይያዙ ፡ ሲሉ ፡ የሸመገለውን ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የደከመውን ፡ ከመካከላቸው ፡ መርጠው ፡ በቀሩት ፡ ፊት ፡ ይገድሉት ፡ ነበር ። ሌሎቹም ፡ ይህንን ፡ በማየት ፡ ፍርሃት ፡ ኃይል ፡ እየጨመረላቸው ፡ በግሥገሣ ፡ ይነዱላቸዋል ።

አንዳንዶቹም ፡ ባርያ ፡ ፈንጋዮች ፡ ባርያ ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ይልቁንም ፡ በየዳር ፡ አገሩ ፡ በሚገኙት ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ አደጋ ፡ እየጣሉ ፡ ግማሾቹን ፡ ገድለው ፡ የተረፉትን ፡ ይወስዱቸዋል ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ብዙዎቹን ፡ ዐመፀኞች ፡ የሆኑ ፡ ባርያ ፡ ፈንጋዮች ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ስለቀጧቸው ፡ አዋጁ ፡ እንደቀድሞው ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ መንግሥት ፡ በቁርጥ ፡ አሳብ ፡ የተነሣበት ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ ዐመፀኞቹ ፡ ስለተረዱት ፡ የባርያ ፡ ንግድ ፡ በቶሎ ፡ ለመጥፋት ፡ ቻለ ። ለምሳሌ ፤

፩ ፡ ሐምሌ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. ሺፈራው ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ በሽፍትነትና ፡ ይልቁንም ፡ በባርያ ፡ ፈንጋይነት ፡ ተይዞ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ከችሎት ፡ ቀርቦ ፡ የሽፍትነት ፡ ሥራ ፡ መሥራቱንና ፡ አምሳ ፡ ባሮች ፡ ከወላሞ ፡ አምጥቶ ፡ መሸጡን ፡ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ አሽከሮቹ ፡ እሱ ፡ በተያዘበት ፡ ጊዜ ፡ ሌሎች ፡ አምሳ ፡ አምስት ፡ ባሮች ፡ ሊሸጡለት ፡ ወደ ፡ ጨርጨር ፡ መሄዳቸውን ፡ ስላመነ ፡ ሊሰቀል ፡ ተፈርዶበት ፡ ተሰቀለ ።

፪ ፡ ወልዴ ፡ ማርያም ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ በባርያ ፡ ፈንጋይነት ፡ ኅዳር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ. ም. ከአፈ ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ፡ ችሎት ፡ ቀርቦ ፡ አርባ ፡ ጅራፍ ፡ ተገርፎዋል ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በሞትም ፡ በግርፋም ፡ ተቀጥተዋል ።

፫ ፡ ወልዴ ፡ ሥላሴና ፡ ቦርጋኔ ፡ ባርያ ፡ ፈንግለው ፡ ለመሸጥ ፡ ሲሄዱ ፡ ሐር ፡ አምባ ፡ እመበረት ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ተያዙ ፡ አንያዝም ፡ በማለት ፡ ተታኩሰው ፡ ሰው ፡ ስለገደሉና ፡ ባርያ ስለፈነገሉ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ በ፲፱፻፲፬ ፡ ዓ. ም. ተሰቅለዋል ።



፬ ፡ ባቴ ፡ የሚባል ፡ ባርያ ፡ እየፈነገለ ፡ ይሸጣል ፡ ቤት ፡ እያቃጠለ ፡ ሰው ፡ ይቀማል ፡ ተብሎ ፡ ተይዞ ፡ ይህንንም ፡ ማድረጉን ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ መስክሮበታልና ፡ ከምባታ ፡ ወርዶ ፡ ይሰቀል ፡ ተብሎ ፡ በ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ. ም. ተፈርዶበታል ። እንደዚሁም ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፤

፭ ፡ አብችና ፡ ኩማ ፡ የሚባሉ ፡ ባርያ ፡ ፈንግለው ፡ መሸጣቸውንና ፡ ሰውም ፡ ገድለዋል ፡ ተብሎ ፡ ስለተመሰከረባቸው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶባቸዋል ።

፮ ፡ ባላምባራስ ፡ ድረሴ ፡ ባርያ ፡ ፈንግሎ ፡ ሸጧል ፡ ተብሎ ፡ ስለተመሰከረበት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልኩ ፡ ይታሠር ፡ ተብሎ ፡ ተፈርዶበታል ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በዚሁ ፡ አዋጅ ፡ ባርነትን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በማስወገዳቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ እንደሠሩላት ፡ በሙሉ ፡ ለመገንዘብ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ማሰብ ፡ አለብን ።

አንድኛ ፡ የቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የገጠማቸውን ፡ ችግር ፡ ማስተዋል ። ሁለተኛ ፡ በሥልጣኔ ፡ ረገድ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ እንደሆነ ፡ መረዳት ። የባርነት ፡ መወገድ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ።

የባርያ ፡ ነፃነት ፡ በአውሮፓ ፡ ቅኝ ፡ አገሮችና ፡ በአሜሪካኖች ፡ ዘንድ ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ሠራተኛ ፡ ሁሉ ፡ በደመወዝ ፡ እንዲሠራ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በአሜሪካ ፡ አገር ፡ ከእርሻና ፡ ከአታክልት ፡ የተገኘው ፡ ሀብት ፡ ቀድሞ ፡ ባሮች ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ይገኝ ፡ ከነበረው ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ የኤኮኖሚ ፡ ኤክስፐርቶች ፡ መስክረዋል ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኃይል ፡ ጨቁነው ፡ ባሮቹን ፡ ቢያሠሩዋቸው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሰዎች ፡ ናቸውና ፡ መንፈሳቸው ፡ ስለማይገዛ ፡ የተቻላቸውን ፡ ያህል ፡ እየለገሙ ፡ በነፃነት ፡ መንፈስ ፡ የሚሠሩትን ፡ ያህል ፡ ስለማይሠሩ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ባሮች ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የተመቸ ፡ ጊዜ ፡ ሲያገኙ ፡ በጌቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይመለሱም ። ምክንያቱም ፡ ተንቀውና ፡ ተጠቅተው ፡ በመኖራቸው ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ቂም ፡ ስለሚያሳድሩ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባርነት ፡ ከገሪቸው ፡ እን ዲጠፋ ፡ በማድረግ ፡ በውስጥም ፡ ሆነ ፡ በውጭ ፡ ፖለቲክ ፡ ረገድ ፡ ትልቅ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ከመሥራታቸው ፡ በላይ ፡ በዋጁ ፡ ውስጥ ፡ እንዳየነው ፡ ነፃ ፡ የወጡት ፡ ባሮች ፡ የሆኑ ፡ ሕፃናት ፡ እየሠሩ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችሉ ፡ ከትም ህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ እንዲማሩ ፡ አድርገውላቸዋል ። ለዚሁ ፡ ማሳሰቢያ ፡ እንዲሆኑ ፡ የዚሁኑ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ፎቶግራፎች ፡ ከዚህ ፡ አግብተናቸዋል ።

በጠቅላላው ፡ የቀሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ከገሪቸው ፡ ባርነትን ፡ ለማጥ ፋት ፡ የደረሰባቸው ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያም ፡ በባሰ ፡ አኳ ኋን ፡ ደርሶባታል ። ጉዳዩም ፡ ፍጻሜ ፡ ለማግኘት ፡ የቻለው ፡ በን ጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ትጋት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተናገር ነው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ልማድ ፡ የሚቀረው ፡ መጀመሪያ ፡ በአእምሮ ፡ አስተያየት ፡ ሰው ፡ ወንድሙን ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ሲገዛው ፡ ነውርነቱ ፡ ባርያ ፡ ሊሆነው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሰ ውን ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ አስተያየት ፡ በማስገመቱ ፡ በጠቅላላው ፡ ለሰው ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ የሚተርፍ ፡ ውርደት ፡ መሆኑን ፡ በማመዛዘን ። ሁለተኛ ፡ በኢኮኖሚ ፡ በኩል ፡ የሚያመጣውን ፡ ጉዳት ፡ በመረዳት ፡ ስለሆን ፡ ይህን ፡ አመዛዝኖ ፡ ከሚያስተውልበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ሕዝብ ፡ ሳይደርስ ፡ በሕግ ፡ ኃይል ፡ ብቻ ፡ ለማስገደድ ፡ ላንድ ፡ መን ግሥት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሚያውክ ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ አስተውለው ፡ ያውሮፓ ፡ ከሳሾችና ፡ ወቃሾች ፡ እውነተኛን ፡ ፍርድ ፡ የሚከተሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተወጡትን ፡ ችግር ፡ አውቀውላቸው ፡ ሊያመሰግኗቸው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ በተደመሰሰና ፡ በተወገደ ፡ ጉዳይ ፡ ሊከሷት ፡ ባልተገባቸው ፡ ነበር ።

በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ሮፓው ያን ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ በባርያ ፡ ጉዳይ ፡ ተከሶ ፡ ሲሰሙ ፡ ኃጢ አቱን ፡ በጣም ፡ የበረታ ፡ የሚያደርጉበት ፡ ምክንያት ፡ ራሳቸው ፡ የሠሩት ፡ ነውረኛ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ትዝ ፡ እያላቸው ፡ በዚያው ፡ ዓይን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቅሉ ፡ ባርነት ፡

ነፃ ፡ የወጡ ፡ የባሮች ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።





ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ።

ነፃ ፡ የወጡ ፡ የባሮች ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።



አንድ ፡ ተማሪ ፡ ከመካከላቸው ፡ ለጓደኞቹ ፡ ያነብላቸዋል ።

ነፃ ፡ የወጡ ፡ የባሮች ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።



የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ ሲማሩ ።

ነፃ ፡ የወጡ ፡ የባሮች ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።



ተማሪዎቹ ፡ ጂምናስቲክ ፡ ሲማሩ ።

ቢኖር ፡ እንኳ ፡ እነሱ ፡ ይሠሩት ፡ ከነበረው ፡ ግፍ ፡ ጋር ፡ የማይመሳሰል ፡ ሁኔታው ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቁት ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ባላስቆጣቸው ፡ ነበር ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባርነትን ፡ ለማስወገድ ፡ ሕዝቤ ፡ የእናንተ ፡ ሕዝቦች ፡ ከደረሱበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ ስጡኝ ፡ ብለው ፡ ለማለት ፡ መብት ፡ ነበራቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰዎች ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ናቸው ። ራሳቸው ፡ የሌላቸው ፡ መልክም ፡ ምግባር ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ እንዲኖር ፡ ይፈልጋሉ ።

በእውነተኛው ፡ ነገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ጌታው ፡ ሀብት ፡ መጠን ፡ ባርያ ፡ ባናናሩ ፡ ይደላው ፡ ነበር ። ባሮች ፡ ባገሩትን ፡ ከጌቶቻቸው ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ ገንዘብም ፡ ከብትም ፡ ይቀበላሉ ። በጌቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ሆነው ፡ ሠርተው ፡ ነግደው ፡ ያተረፉትን ፡ ገንዘብ ፡ ይጠቀሙበታል ። ለጌቶቻቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚያበድሩ ፡ ብዙ ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ። ጌቶቻቸው ፡ ሲሞቱ ፡ እየተናዘዙላቸው ፡ ገንዘባቸውንና ፡ ርስታቸውን ፡ ከዘመዶቻቸውና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ የሚካፈሉበትም ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ባሮችም ፡ ከጨዎች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ይጋቡ ፡ ነበር ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በድብቅ ፡ እንጂ ፡ በይፋ ፡ ከደባባይ ፡ የባርያ ፡ ገበያ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ታሪክ ፡ አይናገርም ። ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ ሕግ ፡ ባይከለክል ፡ ሕዝባችን ፡ በሕሊናው ፡ ይህን ፡ ዐመፅ ፡ ሁልጊዜ ፡ ነውር ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ያስረዳል ። ክፉ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡ የማይታጣ ፡ ጠባይ ፡ ነው ፤ ከሰው ፡ ባሕሪ ፡ የወጣ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ ግን ፡ ነውር ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ለሰው ፡ ሳይሰማው ፡ ሲቀር ፡ ነው ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ መንግሥታችን ፡ በባርያ ፡ ነግዶ ፡ አያውቅም ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለመጣው ፡ ክስ ፡ በላይኛው ፡ ክፍል ፡ እንደተመለከትነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አስፈላጊውን ፡ መልስ ፡ ወዲያው ፡ ሰጥቷል ። ኢትዮጵያ ፡ በዋጅም ፡ በሥራም ፡ ዕድሜ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚገባትን ፡ ስለፈጸመች ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ የምታፍርበት ፡ ነገር ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ እያ ፡ ጅብ ፡ ሳታመከኝ ፡ ብላኝ ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ እኛስ ፡ የምንፈራው ፡ ለምሳሌ ፡ እን

ደታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ አምስትና ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አኤሮፕላኖች ፡ የሚሠሩ ፡ ፋብሪካዎች ፡ የሌሉዋቸው ፡ አገሮች ፡ ነፃነት ፡ አይገባቸውም ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ እንዳይመጣብን ፡ ነው ። ይህም ፡ ቢደረግ ፡ ደግሞ ፡ አያስደንቀንም ። ኢጣልያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የአጥቂነት ፡ ጦርነት ፡ ባነሣች ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ካልሆነ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ የበቃ ፡ ምክንያት ፡ ኖሮዋታል ?



## ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የፈጸሙዋቸው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራዎች ።

አሁን ፡ ግን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሕዝቡን ፡ አስተዳደር ፡ ለማሻሻል ፡ በትጋት ፡ ለተነሡበት ፡ አሳብ ፡ ባርነትን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ማስወገድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የገባርንም ፡ ሁኔታ ፡ እንዳሰቡበት ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ እንመልከት ።

ይህንኑም ፡ ለመረዳት ፡ በየጊዜው ፡ ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የወጡትን ፤ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱትን ፡ አንዳንድ ፡ አዋጆች ፡ ማስታወስ ፡ ይበቃል ።

፩ ፤ ሻለቃ ፡ ( አገረ ፡ ገዢ ፡ ) ወይም ፡ ምስለኔ ፡ ሌሎችም ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ የመንግሥት ፡ ሹሞች ፡ ከንዱ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ በተዘዋወሩ ፡ ጊዜ ፡ ገባር ፡ አንድ ፡ ገንቦ ፡ ጠላ ፤ እሥር ፡ እንጀራ ፡ ለበቅሎ ፤ ወይም ፡ ለፈረስ ፡ አንድ ፤ ወይም ፡ ሁለት ፡ ቁና ፡ ጥሬ ፡ እህል ፡ ( ገፈራ ፡ ) አንድ ፡ ሸክም ፡ ሣር ፡ ወይም ፡ ገለባ ፡ አንድ ፡ ሸክም ፡ እንጨት ፡ ይሰጣል ። የዚህም ፡ ደንበኛ ፡ ስም ፡ መጥን ፡ ይባል ፡ ነበረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደ ፡ ራሲ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ መጥን ፡ እንዲቀር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥተው ፡ ቀርቷል ።

፪ ፤ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ ያገረ ፡ ገዥ ፡ ( ሻለቃ ፡ ) ስንቅ ፡ ካንዱ ፡ ወዳንዱ ፡ አገር ፡ ሲዘዋወር ፡ ገባር ፡ እስከ ፡ አገሩ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ ይሸከማል ። የዚህም ፡ ስም ፡ እልፍ ፡ ይባል ፡ ነበረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ እልፍ ፡ እንዲቀር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥተው ፡ ቀርቷል ።

፫ ፤ አገረ ፡ ገዥ ፡ ሲሾም ፤ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ልዩ ልዩ ፡ ሹሞች ፡ ከመንግሥት ፤ ወይም ፡ ከአገረ ፡ ገዥ ፡ በተሾሙ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ቢለዋወጡ ፡ አንድ ፡ ገባር ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ብር ፤ ወይም ፡ የብር ፡ ግማሽ ፡ ሢሶኛ ፡ ትዳር ፡ ያለው ፡ የብር ፡ ሩብ ፡ ይከፍላል ። የዚህም ፡ ስም ፡ መሾሚያ ፡ ይባል ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አልጋ ፡

ባርያና ፡ ገባር ፡ የሚመሳሰሉትም ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

አንደኛ ፤ አንዳንድ ፡ ገባሮች ፡ ሊከፍሉ ፡ የሚገባቸውን ፡ የመሬት ፡ ግብር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ መክፈል ፡ ሲያቅታቸው ፡ ለግብሩ ፡ ዋጋ ፡ ለውጥ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ባርያ ፡ አድርገው ፡ ይሰጡ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ግብር ፡ የሚቀበሉት ፡ ሹሞች ፡ በመንግሥቱ ፡ ሕግ ፡ ውሥጥ ፡ የሌለውን ፡ ግብር ፡ እየጨመሩ ፡ ባላገሮቹን ፡ በማስጨነቅ ፡ ይበድሉዋቸዋል ። ከዚህም ፡ የባሰ ፡ ደግሞ ፡ መብት ፡ የማይሰጠውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ እያሠሩ ፡ ግፍ ፡ ይውሉባቸው ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ባላገሮች ፡ በየሹሙ ፡ ቤት ፡ እንጨት ፡ ቆርጠው ፡ እየፈለጡና ፤ ከብቶች ፡ እየጠበቁ ፤ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ጭነው ፡ እየተከተሉና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ጥቃቅን ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ በማይገባ ፡ አኳኋን ፡ ሲሠሩ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

እውነት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ግፍ ፡ ሲሠሩበት ፡ ባላገር ፡ ከዳኛ ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ ፍርድ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ እስቲያገኝ ፡ ድረስ ፡ ያለበትን ፡ ድካምና ፡ ችግር ፡ እያመዛዘነና ፡ ከገገሮቹ ፡ ጋር ፡ ግጭት ፡ ማድረግን ፡ እየፈራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በደሉን ፡ ተቀብሎ ፡ መቅረትን ፡ ይመርጥ ፡ ነበር ።

ብዙ ፡ ገባሮች ፡ ደግሞ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ሲያቅታቸው ፡ እንደ ፡ ጭነት ፡ ከብት ፡ እህል ፡ ተሸክመው ፡ ከሲዳሞ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ በማምጣት ፡ ያላገባብ ፡ የግብሩን ፡ ዋጋ ፡ በጉልበታቸው ፡ ይከፍሉ ፡ ነበር ። ይህን ፡ በመሰሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ባርያና ፡ ገባር ፡ የግፍ ፡ ጓደኞች ፡ ሆነው ፡ ኖረዋል ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ በማስተዋል ፡ ባርነትን ፡ ሲያስወግዱ ፡ የገባርም ፡ ጉዳይ ፡ ተሻሽሎ ፡ ባላገር ፡ ለመንግሥት ፡ ብቻ ፡ ግብር ፡ እንዲያገባና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ሁሉ ፡ በደሞዝ ፡ እንዲያድር ፡ ሆኖ ፡ አስገባሪ ፡ በገባር ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ለተቆጣጣሪ ፡ አስቸጋሪ ፡ የነበረ ፡ ሥልጣን ፡ በማስወገድ ፡



ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊያገኘው ፡ የሚገባውን ፡ የነፃነት ፡ መብት ፡ ሲፈጽሙለት ፡ መጋቢት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ. ም. ስለ ፡ መሬት ፡ ግብር ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ወሰኑለት ።

በቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ አገረ ፡ ገገሮች ፡ በሚገዙት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ግብሩን ፡ ራሳቸው ፡ ከሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ተቀብለው ፡ በገቢው ፡ ገንዘብ ፡ ያገርና ፡ የወታደር ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ግብሩን ፡ እየ ተቀበሉ ፡ ወይም ፡ ገባሩን ፡ ለሹምና ፡ ለወታደር ፡ እያከፋፈሉ ፡ ገንዘቡን ፡ በእጃቸው ፡ አድርገው ፡ ያዙበት ፡ ነበር ። ብዙውንም ፡ ጊዜ ፡ እንኳንስ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ ሊሰጡ ፡ አገሩን ፡ ለማስተዳደር ፡አነሰን ፡ እያሉ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ከመንግሥት ፡ ይጠይቃሉ ፡ ወይም ፡ ከባንክ ፡ ይበደሩ ፡ ነበር ።

አገረ ፡ ገገሮውም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በውስጡ ፡ ያሉ ፡ ሹሞች ፡ ገባሩን ፡ ከሕግ ፡ በላይ ፡ ግብር ፡ አምጣ ፡ በማለት ፡ ነጋደውንም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ቀረጥ ፡ ያላገባብ ፡ በማስከፈል ፡ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ባላገሩን ፡ ለራሳቸው ፡ ትርፍ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራላቸው ፡ በማስገደድ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ የሚሠሩበትን ፡ ግፍ ፡ ለመቆጣጠር ፡ ለመንግሥት ፡ አስቸጋሪ ፡ ሥራ ፡ ሆኖበት ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይህንን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሻሽል ፡ ለሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ የሚስማማ ፡ ደንብ ፡ አውጥተው ፡ በሕዝቡ ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ የወደቀበትን ፡ ጉዳት ፡ ለማቅለል ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ዋና ፡ አሳባቸው ፡ ስለነበረ ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከመውረሩ ፡ በፊት ፡ ጨርጨር ፤ ባሌ ፤ ሐረር ፡ ማጂ ፤ ወለጋ ፤ ጂማ ፡ ጎጃም ፡ በእነዚህ ፡ አውራጃዎች ፡ ያሉ ፡ አገረ ፡ ገገሮች ፡ ደሞዛቸውን ፡ ከመንግሥት ፡ እንዲቀበሉ ፤ ባላገሩ ፡ ግን ፡ ለመንግሥት ፡ ብቻ ፡ የተወሰነለትን ፡ ግብር ፡ እንዲያገባ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።

ሠራተኞቻቸውም ፡ የተወሰነ ፡ ደሞዝ ፡ እየተቀበሉ ፡ እንደዛሬው ፡ አገዛዝ ፡ ሰፊ ፡ ደንብ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ አገሩን ፡ ያስተዳድሩበት ፡ ነበር ። ደንቡም ፡ የተሰጠበት ፡ ጽሑፍ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ላስረጂነት ፡ ይገኛል ።

በቀሩትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ ይኸው ፡ ደንብ ፡ እንዲጠናና ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲሠራበት ፡ ታስቦ ፡ ነበር ። ግርማዊነታቸው ፡ የወጠኑዋቸው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሥራዎች ፡ በጠላት ፡ ምክንያት ፡ እንደተቋረጡ ፡ ሁሉ ፡ ይህም ፡ አሳብ ፡ አብሮ ፡ ተቋረጠ ፡ እንጂ ፡ ከጠላት ፡ ወዲህ ፡ የተጀመረ ፡ አዲስ ፡ አሳብ ፡ አለመሆኑን ፡ ያስረዳናል ።

እንደዚሁም ፡ በሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ በሚደረገው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ተካፋይ ፡ እንድትሆን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ፈጽመዋል ።

ከትልቁ ፡ ያለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መከከል ፡ በየጊዜው ፡ የሚነሣው ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ በጦርነት ፡ መወሰኑ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ አገሮች ፡ ስለተስማሙበት ፡ ያለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ የመንግሥታት ፡ ጉባኤ ፡ በጀኔቭ ፡ አቁመው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሆኑ ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በዚህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ በያዘ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አብራ ፡ እንድትገኝ ፡ በብዙ ፡ ደክመው ፡ ማኅበረተኛ ፡ እንድትሆን ፡ አደረጉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ የጦርነት ፡ መቆስቆሻ ፡ የሆነውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ታላላቆች ፡ ያለም ፡ መንግሥታት ፡ እንዳይሠሩ ፡ ለመከልከል ፡ ወጥኖት ፡ የነበረውን ፡ አሳብ ፡ ሳይፈጽመው ፡ በመቅረቱ ፤ በጃፓንና ፡ በሺና ፡ መካከል ፡ የተነሣውንም ፡ ጦርነት ፡ ማስወገድ ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ባለመቻሉ ፤ ጀርመንና ፡ ጃፓን ፡ ከማኅበሩ ፡ በመውጣታቸውና ፡ ወደፊት ፡ ለሚነሱት ፡ እምቢተኞች ፡ በር ፡ በመክፈታቸው ፡ ማኅበሩ ፡ የተቋቋመበት ፡ መሠረት ፡ ዋዘቀ ። በመጨረሻም ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ስለወረረች ፡ ያለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ግፈኛዋ ፡ ኢጣሊያ ፡ መሆኗን ፡ እየተረዱትና ፡ ነገሩም ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ እየታየ ፡ ማኅበሩ ፡ በጥፋተኛዋ ፡ ፋሺስታዊ ፡ ኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ የሚገባትን ፡ ቅጣት ፡ ሳይፈጽም ፡ በመቅረቱና ፡ ጦርነቱም ፡ እንዲቆም ፡ ለማድረግ ፡ ባለመቻሉ ፡ ተደርጎበት ፡ የነበረው ፡ ተስፋ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ታየ ። ያለም ፡ ሰላም ፡ በግፈኞች ፡ መንግሥታት ፡ የሚበጠበጥበት ፡ ጊዜ ፡ ስለመጣ ፡ የመሥዋዕትነትን ፡ ጽዋ ፡ ለመ



ቀበል ፡ የቀዳሚነቱ ፡ እጣ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ደረሰባት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እሷ ፡ ተቀዳሚ ፡ ብትሆን ፡ የጽዋው ፡ ተራ ፡ ለሁሉም ፡ አልቀረለትም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ የቤንዚን ፡ (አምባርጐ ፡ ) ስላደረገባት ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ተደርጎ ፡ የነበረው ፡ ተስፋ ፡ ጨርሶ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ።

ደግሞም ፡ እንደዚሁ ፡ በሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ የመብት ፡ ማጥኛና ፡ የፖለቲካ ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ማነኛውም ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ታስቦ ፡ ባሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ አነሳሽነት ፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. . . . ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ የተፈራረሙበት ፡ የኬሎግ ፡ ውል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ስምምነት ፡ ተደረገ ። ይህ ፡ ውል ፡ የሥልጣኔ ፡ አሳብ ፡ የሚገኝበትና ፡ ያለም ፡ ሰላም ፡ የሚጠበቅበት ፡ መሆኑን ፡ በማስተዋል ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢትዮጵያም ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ከቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ እንድትፈራረም ፡ አደረጉ ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ ስለሠሩላት ፡ እንደ ፡ ብዙዎቹ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ ስላገሩቸው ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ ሁሉ ፡ « እኔ ፡ ትንሽ ፡ ሆነሽ ፡ ነበር ፡ ያገኘሁሽ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ትልቅ ፡ አደረግሁሽ ፡ »ለማለት ፡ ይችላሉ ።

የአእምሮ ፡ ዓይን ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሠሩላትን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ ከታሪክ ፡ ጋር ፡ እያመዛዘነ ፡ በሙሉ ፡ ዋጋው ፡ ሊገምተው ፡ ይችላል ። የዓለም ፡ ታሪክ ፡ ከነሐተታው ፡ ጠንቅቆ ፡ ያላወቀ ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ ሊረዳው ፡ ባለመቻሉ ፡ የተጐዳ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመታት ፡ ጀምራ ፡ ነፃነትዋን ፡ ጠብቃ ፡ የምትኖር ፡ አገር ፡ በመሆኗ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ትልቅነቷን ፡ እንዳላጣች ፡ ማንም ፡ አይስተውም ።

የአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ዛሬ ፡ ያልሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሊኖር ፡ አይገባውም ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ ያደረባቸው ፡ ይመ

ስላሉ ። ባንድ ፡ በኩል ፡ አልሠለጠኑም ፡ እያሉ ፡ እኛንና ፡ ሌሎቹንም ፡ ደካሞቹን ፡ እየወነጀሉን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለሥልጣኔ ፡ በምናደርገው ፡ መጣጣር ፡ ተሰናክለን ፡ እንድንወድቅ ፡ ያደናቅፉን ፡ ነበር ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የበጎ ፡ አሳብ ፡ ምልክት ፡ እያሳዩ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚሠሩት ፡ ግን ፡ የተንኰልና ፡ የሸር ፡ ሥራ ፡ ስለሆነ ፡ በእውነቱ ፡ ነገር ፡ ኃይለኞቹ ፡ መንግሥታት ፡ በደካሞቹ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንደሚያስቡ ፡ በትክክል ፡ ለማወቅ ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ።

እነሱ ፡ ብዙውን ፡ ጐሣ ፡ እየተሰበሰበ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ሲጣጣሩ ፡ የኛን ፡ አገር ፡ እንድትለያይ ፡ ለማድረግ ፡ በመጣጣራቸው ፡ ለመግዛት ፡ መከፋፈል ፡ ያሻል ፡ የተባለው ፡ እንዲሞላ ፡ ለማድረግ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ቆይቷል ። በውጭ ፡ ፖሊቲካ ፡ በኩል ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የገጠሟት ፡ ሁኔታዎች ፡ በዚህ ፡ የተመሩ ፡ ሆነው ፡ ኖረዋል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። አሁን ፡ ግን ፡ ለወደፊቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሠልጠን ፡ የምታደርገው ፡ መጣጣር ፡ የተቃና ፡ አካሄድ ፡ እንዲያገኝ ፡ ከልብ ፡ በሆነ ፡ የመረዳዳት ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩላት ፡ ባሳብም ፡ በሥራም ፡ ይደግፉዋታል ፡ ስንል ፡ በጣም ፡ እንመኛለን ።

ኢትዮጵያ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ባሕርን ፡ በመርከብ ፡ እየተሻገረች ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ እየመሠረተች ፡ ሕዝቦች ፡ እያሠለጠነች ፡ ሐውልት ፡ እያቆመች ፡ ዓለም ፡ ከድንቁርና ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዲራመድ ፡ የረዳች ፡ መንግሥት ፡ ስለሆነች ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በተራዋ ፡ ዓለም ፡ ሊረዳት ፡ ይገባል ።

የኢትዮጵያ ዕድል ፡ ሁልጊዜ ፡ በነጻነቷ ፡ ጸንታ ፡ ራሷ ፡ እየተጣጣረች ፡ የመሠልጠን ፡ ሥራዋን ፡ እንድትፈጽም ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ እንደሰጣት ፡ ማንም ፡ አይስተውም ።

ለምሳሌ ፡ በቦሱዬ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኘው ፡ ስልመናስር ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እሥራኤላውያንን ፡ በወጋቸው ፡ ጊዜ ፡ ሳባኮን ፡ ወይም ፡ ሶዋ ፡ (ሳውስ ፡) የሚባል ፡ ትልቅ ፡ ጠረኛ ፡ የሆነ ፡



የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ግብፅን ፡ ወርሩዋት ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ የእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሆሼአ ፡ የሚባለውም ፡ ከዚሁ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ እርዳታ ፡ ይደርስልኛል ፡ ሲል ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። ይህንኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሶዋ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ይለዋል ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልእ ፡ ም. ፲፯ ፡ ቍ. ፬ ። ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ትልቅነት ፡ የሚገልጥ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ በጥንት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የተነሣንበት ፡ ጉዳይ ፡ ሌላ ፡ ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ትልቅነት ፡ ለመግለጥ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ እናገኛለን ፡ ስንል ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

አሁን ፡ ግን ፡ የተራሮች ፡ ምሽግነት ፡ ዋጋ ፡ ባጣበት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በማያስተማምንበት ፡ ከህጉሮች ፡ መራራቅ ፡ የተነሣ ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ ፈጣን ፡ መርከቦችና ፡ አኤሮፕላኖች ፡ እንዲወገድ ፡ ባደረጉበት ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ጐረቤቶቹ ፡ በልጠውት ፡ የተገኘ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ ነፃነት ፡ አለኝ ፡ ለማለት ፡ አልቻለም ። በሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ነፃነቱን ፡ አስከብሮ ፡ ለመኖር ፡ ቢፈልግ ፡ አውሮፖች ፡ ወደ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በሚጠጋ ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ ባደረጉት ፡ እርምጃ ፡ ከደረሱበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ጥሮ ፡ ግሮ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መድረስ ፡ አለበት ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ የመንፈስ ፡ ተጋድሎ ፡ ላለበት ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፡ በጥበቡ ፡ መርጦ ፡ ላገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሰጣት ፡ ንጉሥ ፡ በመሆናቸው ፡ በቶሎ ፡ እድትሠለጥን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አልነሷትም ። በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ከግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ኖሮዋታል ? ዛሬ ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ ፓርለማ ፡ አላት ፡ ከዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ጉባኤ ፡ ተካፈለች ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶቿ ፡ ከትልቅ ፡ ወይንም ፡ ከትንሽ ፡ መወለዳቸው ፡ ሳይታይ ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይለይ ፡ እንደ ፡ እውቀታቸውና ፡ እንደ ፡ ሙያቸው ፡ መጠን ፡ ከከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ይደርሳሉ ። ይህንንም ፡ ዋና ፡ የዲሞክራሲ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ መብት ፡ ለማግኘት ፡ ለቀሩት ፡ አገሮች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ብርቱ ፡ ትግል ፡ እንደፈጀባቸው ፡ የታሪክን ፡ እርምጃ ፡ የተከታተለ ፡

ሰው ፡ አይስተውም ፤ በጅሮንድ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያትም ፡ ፓርለማ ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ በተናገሩት ፡ ዲስኩር ፡ በሰፊው ፡ ገልጸውታል ።

የትምህርት ፡ ቤቶችም ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ እየተስፋፉ ፡ ያድራሉ ። ኡኒቬርሲቲም ፡ ለማቆም ፡ አሳቡ ፡ ተጠንቶ ፡ ተዘጋጅቷል ። የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ እውቀት ፡ እየጨመሩ ፡ የሚያድሩበት ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችና ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤቶች ፡ ተቋቁመዋል ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ትህምርት ፡ ለመማር ፡ ብዙ ፡ ሕፃናት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ በትምህርታቸው ፡ ተመስግነዋል ። ይህም ፡ ሁሉ ፡ የሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚጉድላቸው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ የወጠኑትን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችሉበት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ የሰላምና ፡ የፀጥታ ፡ ጊዜ ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ያለ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይቻልም ።

ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ያቋቋሙላት ፡ የሥልጣኔ ፡ መሠረቶች ፡ ከእነሱ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጡ ፡ ሕዝቧ ፡ ተስማምተው ፡ በመኖርና ፡ ተብብረው ፡ በመሥራት ፡ ውሳጣዊ ፡ ፀጥታን ፡ ልታገኝ ፡ ያሻታል ። ከውጭም ፡ እንደዚሁ ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃዋን ፡ የሚያሰናክል ፡ ምቀኛ ፡ የሆነ ፡ ጠላት ፡ እንዳይነሳባት ፡ ያስፈልጋል ።

አንድ ፡ መንግሥት ፡ በምስትና ፡ ባሥር ፡ ዓመት ፡ ሊሠለጥን ፡ አይችልም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ረጅም ፡ የሰላምና ፡ የጸጥታ ፡ ዘመን ፡ ያስፈልገዋል ።

ሙሴ ፡ ዠንዴስም ፡ የሚባሉ ፡ የፈረንሣዊ ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ ደራሲ ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ አገራችን ፡ ሲመጡ ፡ የመንግሥትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ በመንግሥትም ፡ የተቋቋሙትን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሥራዎች ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፤ «ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አውሮፓ ፡ ከወደቀችበት ፡ የጥፋት ፡ ሁኔታ ፡ አንሰራርታ ፡ እንደትነሣ ፡ ለማድረግ ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ አውሮፓውያን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ብርቱ ፡ ችግር ፡ እንዳለብን ፡ ማሰብ ፡ አለብን ። ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ በመሥራታቸው ፡ ሁላችንም ፡ ልናደንቃቸውና ፡ በተቻለን ፡ መጠን ፡ ልንረዳቸው ፡ ይገባናል» ። ብለው ፡ አጫወቱን ።



እኒህ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለመጡ ፡ ኢትዮጵያም ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይዙና ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ የነበረችበትን ፡ ሁኔታ ፡ ባይናቸው ፡ ያዩ ፡ ምስክር ፡ ስለሆኑ ፡ እውነተኛ ፡ አሳባቸውን ፡ ሲገልጡልን ፡ ከንጹሕ ፡ ሕሊና ፡ የመነጨ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ ነበር ። አገራቸውም ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ አዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ድካም ፡ ያላቸውን ፡ ይህንኑ ፡ እውነተኛ ፡ ስሜት ፡ በየጋዜጣው ፡ በሚጽፉት ፡ አርእስት ፡ እየገለጡ ፡ አንባቢዎቻቸው ፡ እንዲረዱት ፡ ከማድረግ ፡ አል በዙሩም ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ኢጣሊያ ፡ በምቀኝነት ፡ ያነሣችው ፡ ጦርነት ፡ ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ እንዳሰናከለባቸው ፡ አንዘነጋውም ። ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሊሠራ ፡ የሚገባው ፡ የውለታ ፡ መላሽነት ፡ ሥራ ፡ ምንድነው ?

ማናቸውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ነፃነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንዲሆን ፡ በሥልጣኔ ፡ መንገድ ፡ ሕዝቦች ፡ በሚያደርጉት ፡ እሽቅድምድም ፡ እንዳይበለጥና ፡ የሰነፈ ፡ ሆኖ ፡ እንዳይገኝ ፡ የትምህርቱን ፡ እርምጃ ፡ ማፋጠን ፡ ግዴታ ፡ አለበት ፡ ብለናል ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መድኃኒት ፡ የለምና ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጥንታዊነቷና ፡ በክርስቲያንነቷ ፡ ሕዝቧ ፡ ያገኘው ፡ አዲስ ፡ የተቋቋሙ ፡ ሕዝቦች ፡ ሊያገኙት ፡ የማይችሉት ፡ የትልቅ ፡ ሕዝብ ፡ ጠባዮች ፡ የሆኑት ፡ ዘመን ፡ አመጣሽ ፡ በሆኑ ፡ በማይረቡና ፡ በማይጠቀሙ ፡ ፈሊጦች ፡ እንዳይደመሰሱ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባል ።

ለምሳሌ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በተፈጥሮ ፡ ያላቸው ፡ የተመልካችነት ፤ የትዕግሥተኛነት ፤ የሰው ፡ አክባሪነት ፤ የርኅሩኅነት ፤ የወታደርነት ፤ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ የማይናወጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ እምነት ፡ ትልቅ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ በብዙ ፡ ትምህርት ፡ ሊያገኙት ፡ ስለማይችሉ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሊበላሽ ፡ አይገባም ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ያንድ ፡ ሕዝብ ፡ ትልቅነት ፡ የተመሠረተበት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፤ እየተሻሻለና ፡ ይበልጥ ፡ የጠና ፡ እየሆነ ፡ እንጂ ፡

እየጠፉና ፡ እየተረሳ ፡ በነዚሁም ፡ ቦታ ፡ የማይረባ ፡ ጠባይና ፡ አመል ፡ እየተተካ ፡ እንዳይሔድ ፡ መጠባበቅ ፡ ተምረናል ፡ የሚሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሊያስቡበትና ፡ ሊደክሙበት ፡ የሚገባ ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ሊሆን ፡ ያሻል ።

ለምሳሌ ፡ በሠለጠኑ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ዛሬ ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ እየተናቀና ፡ እየተነቀፈም ፡ ሄዷል ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ጥልቅ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ለመምሰል ፡ ሃይማኖትንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲነቅፉ ፡ ይታያሉ ። አንዳንድ ፡ ፈላስፎችና ፡ (የሲያንስ ፡) ሊቃውንት ፡ የሚያመጡት ፡ ጥርጣሬና ፡ መመራመርን ፡ በማይሆን ፡ መንገድ ፡ የሚወስድ ፡ አሳብ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከመንቀፍ ፡ ያደርሳል ። በእውነቱ ፡ ተመልከቶ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ የእነሱ ፡ ጥበብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቦታ ፡ ሊተካ ፡ የሚችል ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንደማይሰጥ ፡ በቶሎ ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል ።

ስለዚህ ፡ ትምህርትና ፡ ሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ሲገቡ ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ መልክሙን ፡ ጠባይ ፡ እንድንቀስምና ፡ በውስጣችን ፡ የሚገኘውንም ፡ ጉዳት ፡ የሆነብንን ፡ መጥፎ ፡ አመል ፡ እንድናስወግድ ፡ ሊሆን ፡ ያሻል ።

በዓለም ፡ ላይ ፡ ታላላቅ ፡ እውቀት ፡ እየገለጡ ፡ ለሥልጣኔ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ከሠሩት ፡ ሊቃውንት ፡ አንዱ ፡ ኒውተን ፡ ነው ። ኒውተን ፡ በማቴማቲክ ፡ በፊዚክ ፡ በአስትሮኖሚ ፡ (የከዋክብት ፡ ጥበብ ፡) በፍልስፍና ፡ የተመሰገነና ፡ በጣም ፡ የተከበረ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሊቅ ፡ ነው ።

ገና ፡ በልጅነቱ ፡ ኧክሊድ ፡ የሚባለው ፡ የገሮሜትሪ ፡ ሊቅ ፡ የሆነው ፡ የግሪክ ፡ መምህር ፡ የገለጠውን ፡ የሒሳብ ፡ መንገድ ፡ መርምሮ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳሆን ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ደረሰበት ። ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ከራሱ ፡ አመንጭቶ ፡ ሠራ ። ለምሳሌ ፡ በነፋስ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ የወፍጮ ፡ መኪና ፤ ሰው ፡ ሳይመራው ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ እየተንቀሳቀሰ ፡ የሚሄድ ፡ ሠረገላና ፡ በውሃ ፡ የሚሄድ ፡ ሰዓት ፡ ገና ፡ በልጅነቱ ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ። ስለ ፡ መሬት ፡ ምን ፡ ሥርዓት ፤ ስለ ፡ ብርሃን ፡ ጠባይ ፤ የቴሌስኮፕን ፡ አሠራር ፡ ስለ ፡ ማሻሻል ፤ ስለ ፡



ባሕር ፡ መሙላትና ፡ መሸሽ ፤ ስለ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ምሥጢር ፤ ኒውተን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ገልጧል ። እሱ ፡ በገለጠው ፡ ዕውቀት ፡ ጠቢብ ፡ የነበረው ፡ የሰዎች ፡ አሳብ ፡ ሰፊ ፡ አስተያየት ፡ ሊያገኝ ፡ ቻለ ። ስለ ፡ ብርሃን ፡ ጠባይ ፡ ያደረደረገውን ፡ ምርመራና ፡ የገለጠውን ፡ አዲስ ፡ ዕውቀት ፡ ከመመልከት ፡ የተነሣ ፡ የእንግሊዝ ፡ ባለቅኔና ፡ ፈላስፋ ፡ የሆነ ፡ ፖፕ ፡ የሚባለው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጻፈ ፡ ከብዙ ፡ የጨለማ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፤

እግዚአብሔር ፡ አለ « ኒውተን ፡ ይሁን » ብርሃንም ፡ ሆነ ።

ላይብኒትዝ ፡ የሚባለውም ፡ የጀርመን ፡ ፈላስፋ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ኒውተን ፡ ተናገረ ። «ኒውተን ፡ ብቻውን ፡ በማቴማቲክ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ተሰብስቦ ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ተደርጎ ፡ ከሱ ፡ በፊት ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እሱ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ የማቴማቲክ ፡ ሊቃውንት ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ተከማችቶ ፡ ቢመዛዘን ፡ ኒውተን ፡ ብቻውን ፡ የሠራው ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፡ » እነሆ ፡ ኒውተን ፡ በዕውቀቱ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ የሚገመት ፡ ሰው ፡ ነው ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀት ፡ እንደምን ፡ አገኘኸው ፡ ብለው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በመደነቅ ፡ ሲጠይቁት ፡ «ምንም ፡ አይደለም ፡ እኔ ፡ ከትልቁ ፡ የእውነት ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ሆነው ፡ ጠጠር ፡ እየለቀሙ ፡ እንደሚጫወቱ ፡ ሕፃናት ፡ ነኝ ፡» ብሎ ፡ ኒውተን ፡ በትሕትና ፡ ይመልስላቸው ፡ ነበር ።

ትልቅ ፡ የቴሌስኮፕ ፡ (መነጥር ፡) ሠርቶ ፡ ከዋክብትን ፡ ይመረምር ፡ ነበር ። ፕላኔቶች ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ የሚዞሩ ፡ መሆናቸው ፡ መቸም ፡ ከኮፐርኒክ ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ። ኒውተን ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አገኘ ። ይኸውም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ፕላኔቶች ፡ በፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ ስለሚዞሩ ፡ ፀሐይ ፡ የፍጥረት ፡ ዓለም ፡ እምብርት ፡ ነች ፡ ተብሎ ፡ ይታመናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኒውተን ፡ የኛዪቱ ፡ ፀሐይ ፡ በሌላዪቱ ፡ ፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ እንደምትዞር ፡ ያች ፡ ደግሞ ፡ ከብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ከዋክብቶቿ ፡ ጋር ፡ በሌላ ፡ ፀሐይ ፡ ዙሪያ ፡ በበኩሏ ፡ እንደምትዞርና ፡ እንደዚሁም ፡ እያለ ፡ አንዱ ፡ ፀሐይ ፡ ባንዱ ፡ ዙሪያ ፡ በመዞር ፡ ቍጥራቸው ፡ እየቀጠለ ፡ እንደሚሄድና ፡ ፍጻሜውም ፡ የማይደረስበት ፡ ሆኖ ፡ ያንድነት ፡ ሥራት ፡ እንዳላቸው ፡ ተመ

ለከተ ። ይህንን ፡ አዲስ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ በመደነቅ ፡ ተሸበረ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ይህን ፡ ወሰን ፡ የሌለውን ፡ ዓለም ፡ የሠራ ፡ ጌታ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የአክብሮትና ፡ የትሕትና ፡ ስሜት ፡ በልቡ ፡ አደሮበት ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያትና ፡ በምንም ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ በተናገረ ፡ ቁጥር ፡ ሁልጊዜ ፡ ባርኔጣውን ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ሳያነሣ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ደፍሮ ፡ አይጠራም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ዕውቀት ፡ ሰውን ፡ ይልቁንም ፡ በእግዚብሔር ፡ ፊት ፡ የበለጠ ፡ ትሁት ፡ እንጂ ፡ ባለጌ ፡ ወይም ፡ አጉል ፡ ደፋር ፡ ሊያደርገው ፡ አይገባም ። ያገራችን ፡ ሰዎች ፡ ሥልጣኔን ፡ ሲጀምሩ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ አብነት ፡ እንዲከተሉ ፡ እንመኛለን ።



## የሁከት ፡ ዘመን ።

ብዙዎች ፡ አገሮች ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃቸውን ፡ የፈጸሙት ፡ በተመቸ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ሌሎች ፡ ከሷ ፡ በሥልጣኔ ፡ በጣም ፡ አልፈው ፡ በተራመዱበትና ፡ ዓለም ፡ በታወከበት ፡ ዘመን ፡ ከሥልጣኔ ፡ ጋር ፡ ስለተገናኘች ፡ ሌሎቹ ፡ ያልደረሰባቸው ፡ ችግር ፡ ደርሶባታል ። አሁን ፡ ዓለም ፡ ያለችበት ፡ መጥፎ ፡ የሁከት ፡ ዘመን ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ ለመረዳት ፡ በየጋዜጣው ፡ የሚጻፈውንና ፡ በየራዲዮኑ ፡ የሚነገረውን ፡ መገንዘብ ፡ ይበቃል ። ያዛሬውን ፡ ዘመን ፡ ሁኔታ ፡ የተመለከተ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የባቤል ፡ ዘመን ፡ ብሎ ፡ ሰይሞታል ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደተነገረው ፡ የባቤልን ፡ ግንብ ፡ ( ጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ ) ለመሥራት ፡ አስበው ፡ ሰዎች ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ ቋንቋቸውን ፡ ለዋወጠባቸው ። አንዱ ፡ ጓደኛውን ፡ አፈር ፡ አቀብለኝ ፡ ሲለው ፡ ድንጋይ ፡ ይሰጠዋል ። ውሃ ፡ ስጠኝ ፡ ለሚለውም ፡ እንጨት ፡ ያቀብለዋል ። ደራሲው ፡ ሲናገር ፡ ዛሬ ፡ በጊዜያችን ፡ በመንግሥታትና ፡ በሕዝቦች ፡ መከከል ፡ የሚሠራው ፡ እንደዚያው ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ይላል ። ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ራዲዮ ፡ ከአራቱ ፡ የዓለም ፡ ማዕዘን ፡ ሲለፈልፍ ፡ ይውላል ። ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ጋዜጣዎች ፡ እየታተሙ ፡ ለዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ይታደላሉ ። ይህም ፡ ሁሉ ፡ መደረጉ ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ አሳብ ፡ ለአሳብ ፡ እየተከፋፈሉ ፡ እንዲስማሙ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ስምምነት ፡ ከመቸውም ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ ከሰዎች ፡ መከከል ፡ ጠፍታለች ። ቋንቋ ፡ በጣም ፡ በተጣራበትና ፡ በሠለጠነበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ስምምነት ፡ እየጠፋ ፡ ሁከት ፡ በመብዛቱ ፡ የባቤል ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ በጊዜያችን ፡ ደረሰ ፡ ቢባል ፡ ጥርጥር ፡ የለውምና ፡ ደራሲው ፡ ደኅና ፡ ተመልክቷል ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ሰዎች ፡ ምድራዊ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ብቻ ፡ በመፈለግ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ በመራቃቸው ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ክርስቲያኖች ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦችም ፡ ከክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ርቀዋል ፡ መሠረቱ ፡ የሆነው ፡ የወንጌልም ፡ ቃል ፡ ተረስቷል ።

የምትችልበት ፡ የባሕር ፡ በር ፡ መከልከሏ ፡ ነው ። ማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ሥልጣኔን ፡ ከውጭ ፡ ካልተቀበለ ፡ በቀር ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ ሊሠለጥን ፡ እንደማይችል ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ፈረንሳዊ ፡ ክሌ ፡ የሚባለው ፡ ወደቧ ፡ በእንግሊዞች ፡ እጅ ፡ በተያዘበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ እንደተዋጋች ፡ ማሰብ ፡ ነው ። የመስኮብ ፡ ነገሥታት ፡ ይልቁንም ፡ ትልቁ ፡ ጴጥሮስና ፡ ትልቋ ፡ ካቴሪና ፡ በውጭ ፡ ፖለቲካ ፡ ድካማቸው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ በሮቻቸውን ፡ ማስፋፋት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይህንንም በማድረጋቸው ፡ ታሪካቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህም ፡ መሆኑ ፡ ላንድ ፡ አገር ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ማግኘት ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ በመሆኑ ፡ አይደለምን ? ያውም ፡ ደግሞ ፡ ፈረንሳይም ፡ ሆነች ፡ መስኮብ ፡ ከባሕር ፡ ጋር ፡ የሚያገናኟቸው ፡ ሰፊ ፡ አገሮችና ፡ ብዙ ፡ ወደቦች ፡ እያላቸው ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲፈጥራት ፡ ከእነሱ ፡ የሰፋ ፡ እንጂ ፡ ያነሰ ፡ ከባሕር ፡ የምትገናኝበት ፡ አገር ፡ አልነሣትም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ስንት ፡ ባሕር ፡ ቆርጠው ፡ የመጡ ፡ ሕዝቦች ፡ ነጥቀዋት ፡ አንድ ፡ በር ፡ እንኳ ፡ ተከልክላ ፡ የእመቤት ፡ ደሃ ፡ ሆናለች ። ሥልጣኔ ፡ እንዳታገኝ ፡ እንደ ፡ ዋና ፡ ዓይነተኛ ፡ ዘዴ ፡ ተደርጎባት ፡ ይኖራል ። ይህንንም ፡ ችግርዋን ፡ ለዓለም ፡ ከአፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጀምራ ፡ በየጊዜው ፡ እያመለከተች ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አልተደረገላትም ።

ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በቃል ፡ ሳይሆን ፡ በሥራ ፡ የተገለጠ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። የሚገባውን ፡ መብት ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈልግ ፡ ሕዝብ ፡ ኃይል ፡ አለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ ይንጠቅ ፡ ኃይል ፡ ከሌለው ፡ ግን ፡ አፉን ፡ ይዝጋ ፡ እንደማለት ፡ የመሰለ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በእውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ የተማመነች ፡ ስለሆነች ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በፍርድ ፡ ይሰጡኛል ፡ በማለት ፡ ተስፋዋ ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ የጠነከረ ፡ ነው ።

ባሁን ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ሲጉድልበት ፡ ከዓለም ፡ ላይ ፡ እውነት ፡ በመጥፋቷ ፡ ይገርመዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ በሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡ ላይ ፡ የሚሠራውን ፡ ግፍ ፡ ሲያነሡበት ፡ ዓይኖቹን ፡ ጨፍኖ ፡ ጆሮዎቹንም ፡ ይዘጋል ።



በዓለም ፡ ላይ ፡ የልቡን ፡ ለመሥራት ፡ የሚችልና ፡ ሌሎች ፡ ግፍ ፡ እንዳይወሉበት ፡ የማይሠጋ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ የሚመስላቸው ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትልቅ ፡ ሞኝነት ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በማይመረመር ፡ ጥበቡ ፡ ሰዎች ፡ ከእውነት ፡ መንገድ ፡ ርቀው ፡ የኃይልን ፡ መንገድ ፡ ሲከተሉ ፡ የሚያመጣት ፡ ጠንቅ ፡ በኃይለኞች ፡ ላይ ፡ የሚያደርስባቸው ፡ ጥፋት ፡ በደካሞች ፡ ላይ ፡ ከሚያደርስባቸው ፡ ይልቅ ፡ ሺህ ፡ ጊዜ ፡ የከፋ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጓታል ። ስለዚህ ፡ ኃይለኞች ፡ በኃይላቸው ፡ ተመክተው ፡ ምንም ፡ የሚያተርፉት ፡ ነገር ፡ የለም ። ታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ ያሉበት ፡ ሁኔታ ፡ በእርግጥ ፡ ይህ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ «እሁንም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ሲገኝ ፡ እኔ ፡ ጨርሼ ፡ እጠፋለሁ ፡ »ብላ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ ፒሩስ ፡ ለመናገር ፡ ከሚገባት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ደርሳለች ። መንግሥታት ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፡ ትልቅነትን ፡ የሚያገኙት ፡ በኃይላቸው ፡ ወይም ፡ በግዛታቸው ፡ ስፋት ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈጽሙዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ነው ።

ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚመራበት ፡ ዋናው ፡ መንገድ ፡ ትምህርት ፡ መሆኑን ፡ በማስተዋልና ፡ ይኸውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ለክቡር ፡ የትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በየጊዜው ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ እየሰጡ ፡ በተለየም ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ተጠባባቂነት ፡ ሥራው ፡ እንዲካሄድ ፡ ማድረጋቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ አይስተውም ።

ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ ሲነሣ ፡ ከፊታችን ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ይደቀናል ። ይኸውም ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ካልሠለጠነ ፡ ሕዝባችን ፡ እውነተኛውን ፡ የሥልጣኔ ፡ መንገድ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ቋንቋችን ፡ የሚሠለጥነውም ፡ ለትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የሚያስፈልጉና ፡ ጠቃሚነታቸውም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወቀ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ አማርኛ ፡ ሲተረጐሙ ፡ የልብ ፡ ወለድና ፡ የቴአትር ፡ መጻሕፍትም ፡ ሲበዙና ፡ ሲለመዱ ፡ ነው ። ይህን ፡ በመሰለ ፡ አኳኋን ፡ ቋንቋ ፡ ካልተሠራበት ፡ ሊጣራ ፡ አይችልም ። ሕዝብም ፡ የዓለምን ፡ ጥበብ ፡

ባገሩ ፡ ቋንቋ ፡ ካልገለጡለት ፡ የሥልጣኔን ፡ አሳብ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆንበት ፡ መንገድ ፡ አያገኝም ። ለምሳሌ ፡ ባገራችን ፡ የተማሩ ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ቢገኙ ፡ እነዚህም ፡ ትምህርታቸው ፡ በባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ ሲሆን ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሠልጥና ፡ የጥበብንና ፡ የሥልጣኔን ፡ መንፈስ ፡ እየገለጠ ፡ በተማሩት ፡ ሰዎች ፡ ደራሲነትና ፡ ተርጓሚነት ፡ ለሕዝቡ ፡ ካላሰማቻቸው ፡ የመቶ ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ መማርና ፡ መሠልጠን ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ለሚሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚጠቅም ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። በተማሩት ፡ ሰዎችና ፡ በሕዝቡም ፡ መከከል ፡ ትልቅ ፡ ያሳብና ፡ የጠባይ ፡ የምኞትና ፡ የማስተዋል ፡ ልዩነት ፡ ይፈጠራል ። ያማርኛ ፡ መጻሕፍት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ አኳሆን ፡ ሲሠራበትና ፡ መጻሕፍት ፡ ሲጻፉበት ፡ ግን ፡ በተማሩት ፡ ሰዎችና ፡ በሕዝቡ ፡ መከከል ፡ የመንፈስ ፡ ሕብረት ፡ ይመሠረታል ።

ተማሪዎችም ፡ ዛሬ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ በተተረጐሙ ፡ መጻሕፍት ፡ መማራቸው ፡ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ ዕውቀት ፡ በቶሎ ፡ እንዲራመዱ ፡ ረድቷል ። በዚህም ፡ አሳብ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከጠላት ፡ በፊት ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ አስተዋይነት ፡ ታውጆ ፡ የነበረውን ፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እንዲያውቅ ፡ የሚያስገድደውን ፡ አዋጅ ፡ እንዲጸና ፡ ለማድረግ ፡ መታሰቡ ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑ ። አይጠረጥርም ።

በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጐጃምና ፡ ጐንደር ፡ የሊቃውንት ፡ አገሮች ፡ ሆነው ፡ እንደኖሩ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በዘመኗ ፡ የእነሱን ፡ ክብር ፡ እንድትወርስ ፡ የግዕዝና ፡ የአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ እየተደጋገፉ ፡ የዘመናችንን ፡ የሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ ለመቅዳትና ፡ ለመግለጥ ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ የሚያዘጋጁላቸውን ፡ እንደ ፡ ኡኒቬርሲቴና ፡ እንደ ፡ አካዴሚ ፡ ያሉ ፡ ሊደራጁላቸው ፡ ያስፈልጋል ።

ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦቿ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ስለሆነ ፡ ቋንቋዋን ፡ ካላሠለጠነች ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉትን ፡ ሕዝቦች ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ወደሥልጣኔ ፡ ትመራቸዋለች ። የውጭ ፡ አገር ፡ መምህራን ፡ እየቀጠረች ፡ የባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ በማስተማር ፡ ነውን ?



ኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ የሆነች ፡ በሁሉም ፡ ረገድ ፡ ትልቅነት ፡ ያላት ፡ ቋንቋቸውና ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የተለያየ ፡ ሕዝቦች ፡ የምታስተዳድር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ ስለሆነች ፡ ይህንኑ ፡ የተሰጣትን ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ አደራ ፡ በሥልጣኔ ፡ ረገድ ፡ ለመፈጸም ፡ ትልቅ ፡ የመንፈስ ፡ ዝግጅት ፡ ያስፈልጋታል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ የቋንቋዋ ፡ ጉዳይ ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡— ይቀርባል ።

ለምሳሌ ፡ አውሮፖች ፡ በሠለጠኑዋቸው ፡ አንዳንድ ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ እንደሚታየው ፡ ሕዝቡ ፡ የሠለጠነው ፡ በገገሩው ፡ መንግሥት ፡ ቋንቋ ፡ እንጂ ፡ በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ ባለመሆኑ ፡ በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ ነፃነት ፡ ቢሰጠው ፡ እንኳ ፡ ከገገሩው ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ተሳስሮ ፡ መኖር ፡ ግዴታ ፡ ሆኖበታል ።

የጋዜጣ ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ ሊሻሻል ፡ ያስፈልጋል ። ጋዜጣ ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ከጦር ፡ መሣሪያ ፡ አያንስም ። ስለዚህ ፡ መንፈሳቸው ፡ ከሙሉ ፡ ልብ ፡ በሆነ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ፍቅር ፡ የጋለ ፡ ሰዎች ፡ ተመርጠው ፡ በተለየ ፡ የጋዜጣኛነት ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ ማድረግ ፡ በብዙ ፡ ይጠቅማል ።

በዛሬ ፡ ዘመን ፡ የማነኛውም ፡ ሕዝብና ፡ የማነኛውም ፡ መንግሥት ፡ አሳብ ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ የሚገለጠው ፡ በጋዜጦች ፡ ነው ። ለሕዝብም ፡ የጥበብንና ፡ የሥልጣኔን ፡ መንገድ ፡ እያመለከቱ ፡ ትልቅ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡ ፡ ጋዜጦች ፡ ናቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከማንኛውም ፡ የብልጠት ፡ አካሄድና ፡ ከማንኛውም ፡ የተራቀቀ ፡ የፖለቲክ ፡ ስልት ፡ ሁሉ ፡ የሚሻለውና ፡ የሚበልጠው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ጠብቆ ፡ ያኖራት ፡ ጌታ ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷን ፡ እንዳይለያቸው፡ መጸለይና ፡ መለመን ፡ ከሁሉም ፡ ነገር ፡ ይበልጣል ።

አሁን ፡ ወደ ፡ ባርነት ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ። ባርነት ፡ እንዲወገድ ፡ የረዳ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ የመኪና ፡ ዘዴ ፡ መገኘቱና ፡ መስፋፋቱ ፡ ነው ።

## የ ፋ ብ ሪ ካ ፡ ጥ በ ብ ።

በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ስናመዛዝነው ፡ ባርነት ፡ እንዲቀር ፡ የተደረገበት ፡ አንዱም ፡ ምክንያት ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ በመስፋፋቱ ፡ ነው ፡ ብንል ፡ ስሕተት ፡ አይሆንብንም ። የላቦት ፡ ምሥጢር ፡ ተገኝቶ ፡ ፋብሪካዎችን ፡ እንዲያንቀሳቅስ ፡ ማድረግ ፡ በተጀመረ ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ ትልቅ ፡ መለዋወጥ ፡ ሆኗል ። በመኪና ፡ ጕልበት ፡ የሰው ፡ ሀብት ፡ ወሰን ፡ በሌለው ፡ አኳኋን ፡ እያደገ ፡ እንደሚሄድ ፡ ከማንኛውም ፡ አገር ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ የተረዳችው ፡ እንግሊዝ ፡ ነች ። በ፲፯፻፴፰ ፡ ዓ. ም. ሉዊስ ፡ ፖል ፡ የሚባል ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሱፍ ፡ የሚፈትል ፡ መኪና ፡ ሠርቶ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ዶክቶር ፡ ጆምስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ « ፖል ፡ ቢፈቅድ ፡ በአሥር ፡ ሺህ ፡ ስቴርሊንግ ፡ ብቻ ፡ ሥራውን ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ አዲስ ፡ ባወጣው ፡ መኪና ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሎንዶን ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሲቲ ፡ የተባለውን ፡ መንደር ፡ በሙሉ ፡ ለመግዛት ፡ የሚችልበት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ፡ » ብሎ ፡ ተንቢት ፡ ተናገረለት ።

እንግዲህ ፡ እንግሊዝ ፡ ባርነትን ፡ ያስወገደችው ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ ጥቅም ፡ ከታወቀ ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ቈይቶ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

እውነትም ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ፋብሪካ ፡ ያቆሙ ፡ ሰዎች ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ሀብት ፡ አገኙ ። ለምሳሌ ፡ አክራይት ፡ የሚባል ፡ ጠጕር ፡ ቈራጭ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ አቅራቢያ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

እሱም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ መሃይምን ፡ ቢሆን ፡ ምኞቱ ፡ ሁሉ ፡ ሀብታም ፡ ለመሆን ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የንግድ ፡ ጥበብ ፡ በልቡ ፡ አደረበት ። አንድ ፡ ተራ ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የፈትል ፡ መኪና ፡ በጥበብ ፡ ሠርቷል ፡ የማለትን ፡ ወሬ ፡ ስለሰማ ፡ አለበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ፈልጎ ፡ አገኘውና ፡ ሕይወቱን ፡ ሙሉ ፡ ባጠራቀመው ፡ ገንዘብ ፡ የፈትሉን ፡ መኪና ፡ ገዝቶ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ አጽፎ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተቀበለበት ። አክራይት ፡ ካሥር ፡ ዓመት ፡



በኋላ ፡ በዚህ ፡ በፈትል ፡ ፋብሪካ ፡ ግማሽ ፡ ሚሊዮን ፡ ስቴርሊንግ ፡ አትርፎበት ፡ ሞተ ። ይህም ፡ ገንዘብ ፡ ለዚያን ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነበር ።

በዚሁ ፡ ዘመን ፡ አቅራቢያ ፡ ኤድሞንድ ፡ ካትራይት ፡ የሚባል ፡ ባለቅኔ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከሰዎች ፡ ጋር ፡ ሲጫወት ፡ የፈትል ፡ ፋብሪካ ፡ ተገኝቷል ። ይኸውም ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ከሚሠራው ፡ ይበልጥ ፡ በብዙ ፡ ይሠራል ፡ ብለው ፡ ስለነገሩት ፡ የጨርቅ ፡ ፋብሪካ ፡ ሊሠራ ፡ አሰበ ። ካንድ ፡ አናጢና ፡ ካንድ ፡ ብረት ፡ ቀጥቃጭ ፡ ጋር ፡ ተስማምቶ ፡ አሳቡን ፡ እየሰጣቸው ፡ መኪና ፡ አቋቋመ ። አራት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ እየመረመረ ፡ በማሻሻል ፡ ራሱ ፡ ፈትሎ ፡ ጨርቅ ፡ የሚሠራ ፡ አቶማቲክ ፡ መኪና ፡ አበጀ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፋብሪካ ፡ በመላው ፡ አውሮፓ ፡ ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ በጣም ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ። በጥቂት ፡ ዓመታትም ፡ ውስጥ ፡ ጥጥ ፡ ከቀድሞው ፡ ይልቅ ፡ ኀምሳ ፡ ጊዜ ፡ አብልጦ ፡ ተፈለገ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እንግሊዝ ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ ጨርቅ ፡ እየገዛች ፡ ትወስድ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ጨርቅ ፡ በፋብሪካ ፡ ስለሚሠራ ፡ እንግሊዝ ፡ እንኳንስ ፡ ከውጭ ፡ ልታመጣ ፡ ጨርቆቿን ፡ ለሕንድ ፡ አገር ፡ በብዙ ፡ ትሸጥ ፡ ጀመር ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አለመጠን ፡ ገንዘብ ፡ አገኙ ። በ፲፯፻፺፪ ፡ ዓ. ም. አንዱ ፡ ሰው ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ ሲገልጥ ፡ «በትልቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ነፃነትና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ የሕዝቡ ፡ ሀብት ፡ አለመጠን ፡ እያደገ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብም ፡ (ካፒታል) ፡ እየበረከተ ፡ እንዲሄድ ፡ ስላደረጉለት ፡ ዛሬ ፡ ማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሥራ ፡ ቢጀምሩ ፡ እንከሥራለን ፡ ብለው ፡ ሊሠጉ ፡ አይችሉም ።

የሕዝባችን ፡ ጥበበኛነት ፡ ሠራተኛነት ፡ ባለሙያነት ፡ ትጉህነት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ በማናቸውም ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ቢሆን ፡ ያለሥጋት ፡ ነግደው ፡ ሊያተርፉና ፡ ሊከብሩ ፡ ይችላሉ ፡ » ብሎ ፡ ተናገረ ።

ካም ፡ ፍሬ ፡ ነው ። የሮማም ፡ ትልቅነት ፡ የተገኘው ፡ እንደዚሁ ፡ በባሮች ፡ ድካም ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ፋብሪካዎች ፡ ስላሏቸው ፡ የሰው ፡ ድካም ፡ ምንም ፡ አይጠቅማቸውም ። ይልቅስ ፡ በነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ እየተቀጠሩ ፡ ለመሥራት ፡ የገዛ ፡ ሕዝቦቻቸው ፡ ሲፈልጉ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ፋብሪካ ፡ የሚሠራው ፡ በመሆኑ ፡ ሥራ ፡ አጥተው ፡ ተቸግረዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ፋብሪካ ፡ በሰው ፡ ጉልበት ፡ ተተክቶ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውን ፡ ሲሆን ፡ በፋብሪካ ፡ ለሚሠራው ፡ ዕቃ ፡ የሚሆነውን ፡ እንደ ፡ ጥጥ ፤ ብረታ ፡ ብረትና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የመሬት ፡ ሀብት ፡ ማግኘት ፡ ለሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ችግር ፡ ሆኖባቸው ። ስለዚህ ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ እየያዙ ፡ ሕዝቡን ፡ ባገሩ ፡ መሬት ፡ ላይና ፡ በመሬቱም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡ ይወስዱብታል ። ስለዚህ ፡ ባርነት ፡ በቅኝ ፡ አገር ፡ ተለወጠ ፡ ብንል ፡ ስሕተት ፡ አይሆንም ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ባሁኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተከበረ ፡ ሆኖ ፡ ቢታይ ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ ባይገኝ ፡ ኖሮ ፡ ባሮች ፡ ነፃነት ፡ ያገኙ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ ያጠራጥራል ።

አርስጣጣሊስ ፡ ባርያ ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ፡ እያለ ፡ ባርነትን ፡ የሚደግፍ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ብለናል ። ይህን ፡ የምትልበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድነው ፡ ተብሎ ፡ ሲጠየቅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይመልስ ፡ ነበር ። «የሥራ ፡ መሣሪያ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ሲታዘዝ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ሥራውን ፡ ዐውቆ ፡ የሚሠራ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፤ ለምሳሌ ፡ የሸማኔ ፡ መወርወሪያ ፡ የሸማኔ ፡ እጅ ፡ ሳይነካው ፡ ብቻውን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተወረወረ ፡ ሸማ ፡ ቢሠራ ፤ ወይም ፡ ያዝማሪ ፡ መሰንቆ ፡ የሰው ፡ ጣት ፡ ሳይነካው ፡ ብቻውን ፡ ድምፅ ፡ ቢሰጥ ፡ ኖሮ ፤ የሰው ፡ እጅ ፡ ለማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ለማንኛውም ፡ ጥበብ ፡ የማያስፈልግ ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ሕንፃ ፡ የሚሠራ ፡ መሐንዲስም ፡ አናጢዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሠራተኞች ፡ ባላስፈለጉት ፡ ነበር ። ባለቤት ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ሰብ ፡ አባት ፡ የሆነ ፡ ሰውም ፡ አገልጋዮችና ፡ ባሮች ፡ ሊኖሩት ፡ ዘንድ ፡ የሚያሻ ፡ ባልሆነ ፡ ነበር ።» እንግዲህ ፡ አርስጣ



ጣሊስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ የሸማኔ ፡ እጅ ፡ ሳይወረውረው ፡ የሸማኔ ፡ መወርወሪያ ፡ ብቻውን ፡ ሸማ ፡ የሚሠራው ፤ መሬት ፡ በመቆፈር ፡ ግንብ ፡ በማፍረስ ፤ ድንጋይና ፡ አሸዋ ፡ ሲሚንቶም ፡ በማቀበል ፡ ሕንፃ ፡ የሚሠራ ፡ መሐንዲስ ፡ የሠራተኞቹን ፡ አገልግሎት ፡ ከመኪና ፡ የሚያገኝበት ፤ በጠቅላላው ፡ የዛሬው ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ሁሉ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ታውቆ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አርስጣጣሊስ ፡ ስለባርያ ፡ ጉዳይ ፡ ያለውን ፡ አሳብ ፡ ምናልባት ፡ ሳይለወጥ ፡ አይቀርም ፡ ኖሮዋል ?

ይህን ፡ አስተያየት ፡ ማምጣታችን ፡ ባርነት ፡ የተወገደው ፡ የሰውን ፡ መብት ፡ አክብረው ፡ ባርነት ፡ ከለም ፡ ላይ ፡ እንዲፋቅ ፡ የተከራከሩና ፡ የተሟገቱ ፡ ሰዎች ፡ በደረጉት ፡ ትግል ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ በመገኘቱና ፡ የሰው ፡ አገልግሎት ፡ የማይጠቅም ፡ ሆኖ ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ በመታየቱ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይደለም ። ይህ ፡ እንዳይባልማ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ነፃነት ፡ የተከራከሩ ፡ ሰዎች ፡ ያደረጉትን ፡ ትግልና ፡ ያስገኙትንም ፡ ፍሬ ፡ ገልጠነዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብም ፡ ባርነት ፡ እንዲወገድ ፡ ለማድረግ ፡ ሳይረዳ ፡ እንዳልቀረ ፡ ለማስታወስና ፡ ፋብሪካ ፡ ባላቸውና ፡ በሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ የኤኮኖሚ ፡ ልዩነት ፡ ለማሳሰብ ፡ ነው ።

የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ የባርያ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲቀር ፡ ለመርዳቱ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ የበለጠ ፡ ግልጥ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ብንፈልግ ፡ ጆን ፡ ጉንተር ፡ የሚባል ፡ የአሜሪካ ፡ ተወላጅ ፡ በጻፈው ፡ ( በተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ) በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ስንመለከት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ እናነባለን ።

«የእርሻ ፡ ሥራ ፡ በመኪና ፡ በመሠራቱ ፡ ምክንያት ፡ የደቡብን ፡ አገር ፡ እየለቀቁ ፡ የሚወጡት ፡ ጥቁሮች ፡ ቍጥራቸው ፡ እየበዛ ፡ ሄዷል ።

ስለዚህ ፡ የኤክስፔርት ፡ ሰዎች ፡ እንደሚናገሩት ፡ በደቡብ ፡ ክፍል ፡ ከሚሠሩት ፡ ሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ ተኩል ፡ ከሚሆኑት ፡ ጥቍሮች ፡ ወደፊት ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ (ለእርሻ ፡) ሥራ ፡ የሚፈለጉት ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ብቻ ፡ ይሆናሉ ። እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ባገሩ ፡

ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ሚሊዮን ፡ ተኩል ፡ ጥቍሮች ፡ ሲጨመሩ ፡ እነዚህን ፡ መመገብ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ መስጠትና ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መላክ ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ሲል ፡ የሰሜን ፡ ክፍል ፡ አሳብ ፡ ገብቶታል ። »

እነሆ ፡ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ በመስጠቱ ፡ ላሁኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሲረዳ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በላቸውና ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ በሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ልዩ ነት ፡ እንዲፈጠር ፡ አደረገ ። በዚህም ፡ በኩል ፡ ትልልቅ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ያላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ በሀብትና ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ በጠቅላላውም ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ኃይላቸው ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ በሌለው ፡ አኳኋን ፡ እየጨመረና ፡ እያደገ ፡ ሲሄድ ፡ ትልልቅ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ቀድሞ ፡ በነበሩበት ፡ ቦታ ፡ እንዳሉ ፡ በመቅረታቸው ፡ መጠን ፡ በመካከላቸው ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ይበልጥ ፡ እየተራራቀ ፡ ሄዷል ።

ይህም ፡ ሁኔታ ፡ ሞንቴስኪየ ፡ «ዛሬ ፡ (በመንግሥታት ፡ መካከል ፡) ያለው ፡ የኃይል ፡ ሚዛን ፡ ልዩነቱ ፡ አለመጠን ፡ የተራራቀ ፡ በመ ሆኑ ፡ ማናቸውም ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ መንግሥት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከወ ሰነለት ፡ ከትንሽነቱ ፡ ቦታ ፡ በራሱ ፡ አቅም ፡ ብቻ ፡ ተጣጥሮ ፡ ለመ ነሣትና ፡ ለመውጣት ፡ ፈጽሞ ፡ አይችልም ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። » ሲል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ ይለናል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህች ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ኃይል ፡ የተገኘች ፡ የግ ዙፍ ፡ አካል ፡ ሥልጣኔ ፡ እውነተኛዋ ፡ ሥልጣኔ ፡ ነች ፡ ብለን ፡ ከማ መንና ፡ ከማሰብ ፡ ልንጠነቀቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። የዛሬዎቹ ፡ የሠለ ጠኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ (በሲያንስ ፡) ጥበብ ፡ እጅግ ፡ቢራመዱ ፡ በሰብአዊ ፡ ጠባይና ፡ ባሕሪ ፡ በኩል ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይሻሉም ፡ ብንል ፡ ስሕተት ፡ አይሆንብንም ። የሰ ውን ፡ መንፈስ ፡ በማዳኑ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማ ኖት ፡ በብዙ ፡ ቢረዳ ፡ ይህ ፡ ሃይማኖት ፡ ከሚያስተምረው ፡ ትምህ ርት ፡ ሰዎች ፡ እየራቁ ፡ በመሄዳቸው ፡ በአእምሮ ፡ በኩል ፡ በመኻ ሻል ፡ ፊንታ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰዋልና ። በጥንቶቹ ፡ ሮማውያን ፡



ዘንድ ፡ የነበረው ፡ ጨካኝነት ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ አደራ ረግ ፡ ቢሆን ፡ ዛሬ ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ አይገኝም ። የዛሬው ፡ የሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ የበለጠ ፡ ደግነት ፡ ርኅራኄና ፡ ትክክለኛነት ፡ አለው ። በዛሬው ፡ የሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ ያሉ ፡ መንግሥታትም ፡ ለግል ፡ ጥቅማቸው ፡ ሲሉ ፡ የሚ ሠሩት ፡ ተንኰልና ፡ የውሸት ፡ ሥራ ፡ ለምሳሌ ፡ ከጥንቱ ፡ ከሮማዊው ፡ መንግሥት ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የታሪክ ፡ ማስረጃ ፡ እየሰጠ ፡ የሚ ያስረዳን ፡ ሊቅ ፡ እናገኛለንን ? እኔ ፡ እንደ ፡ ራሴ ፡ የሚገኝ ፡ አይ መስለኝም ። ስለዚህ ፡ የእውነተኛዋን ፡ ሥልጣኔ ፡ መንገድ ፡ ዓለም ፡ ገና ፡ አላገኘውም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኢንዱስትሪና ፡ በግ ዙፍ ፡ አካል ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ (በሲያንስ ፡) ጥበብ ፡ በሚገኘው ፡ ሥልጣኔ ፡ ገና ፡ ቢሆን ፡ በአእምሮ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከማንኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ይበልጣል ፡ እንጂ ፡ አያንስም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡ በመሆኑ ፡ ያለው ፡ መልካም ፡ ባሕሪ ፡ ጠባየ ፡ ትልቆች ፡ የነበሩትን ፡ የሆሜርን ፡ ሰዎች ፡ ይመስላል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሩኅሩኅ ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ ባዬ ፡ ምኒልክ ፡ ኋላም ፡ አሁን ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ በኢ ትዮጵያውያን ፡ እጅ ፡ የወደቁ ፡ የኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ በማናቸ ውም ፡ በሌላ ፡ በሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የሚያገኙትን ፡ የምሕረ ትና ፡ የትዕግሥተኛነትን ፡ አያያዝ ፡ በማራኪዎቻቸው ፡ ዘንድ ፡ አግኝ ተዋልና ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳጁን ፡ በእውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ የሚመለ ከት ፡ እውነተኛነትና ፡ የትልቅነት ፡ ጠባይ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚወድ ፡ በእሙንነቱ ፡ ጸንቶ ፡ የሚገኝ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ እውነተኛ ፡ ሥልጣኔ ፡ በግዙፍ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ አለመሆኑን ፡ ያልተረዱና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እው ነተኛ ፡ ጠባይ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ መርምረው ፡ ያላወቁ ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በየጋዜጣውና ፡ በየመጻሕፍት ፡ ላይ ፡ ስሕ ተተኛ ፡ ፍርድ ፡ ይጽፋሉ ።

## ታላላቅ ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ።

ሥልጣኔ ፡ የተከበረችና ፡ የተወደደች ፡ ሰውን ፡ የምታከራ ፡ ውብ ፡ የሆነች ፡ ነገር ፡ ሆና ፡ ስናያት ፡ በድካማቸውና ፡ በትጋታቸው ፡ ሠርተው ፡ ያፈሩዋትን ፡ ሰዎች ፡ በየሙያቸው ፡ ሳናነሣቸው ፡ ልናልፍ ፡ አይገባም ። የሚያምር ፡ ወይም ፡ በጠባዩ ፡ የሚያስመሰግን ፡ ልጅ ፡ ተመልክቶ ፡ አባቱ ፡ ማነው ? ተብሎ ፡ ሳይጠየቅ ፡ አይታለፍም ።

ሥልጣኔ ፡ ለመገኘት ፡ የቢታችው ፡ በጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ዋጋና ፡ ድካም ፡ ነው ። እነሱም ፡ በየዘመኑ ፡ ዕውቀትንና ፡ ጥበብን ፡ በየቅር ንጫፉ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ስጦታቸውና ፡ እንደ ፡ ሙያቸው ፡ መጠን ፡ መንገዱን ፡ ተልመው ፡ ስለ ፡ ሰጡ ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡ እየተመሩ ፡ ሊያስፋፉት ፡ ቻሉ ።

በሥልጣኔ ፡ ውስጥ ፡ ሙዚቃ ፡ ሥዕል ፡ መሣል ፤ ምስል ፡ መቅረጽ ፤ ድርሰት ፤ ቅኔ ፤ እነዚህ ፡ ሙያዎች ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ እንዳላቸው ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ።

«የቬኒስ ፡ ነጋዴ ፡ » በተባለው ፡ ቴአትሩ ፡ ውስጥ ፡ ሻኬስፒር ፡ ስለ ፡ ሙዚቃ ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። « ዚሪዎች ፡ የሆኑ ፡ መንጋ ፡ አውሬዎች ፤ ወይም ፡ ያልተገሩ ፡ ወጣቶች ፡ ፈረሶች ፡ ሲሄዱ ፡ ተመልከቱዋቸው ። የደም ፡ ፍላት ፡ እያነሣሣቸው ፡ ይፈረጥጣሉ ፤ ያስከክሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በድንገት ፡ የጥሩምባ ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ ከጆሮዋቸው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ ሲቆሙ ፡ ታስተውላላችሁ ፤ ቅብዝብዝ ፡ የነበረው ፡ አስተያየታቸውም ፡ ከሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ ከሚገኘው ፡ ደስታ ፡ የተነሣ ፡ በትካዜ ፡ ስሜት ፡ ይፈዛል ። ምንም ፡ ጨካኝ ፤ ምንም ፡ ጠንካራ ፤ ምንም ፡ ኃይለኛ ፡ ቢሆን ፤ ሙዚቃ ፡ ጠባዩን ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ የማይለውጠው ፡ ፍጡር ፡ አይገኝምና ። በሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ የሙዚቃ ፡ ፍቅር ፡ የሌለው ፤ ውብ ፡ የሆነ ፡ የሙዚቃ ፡ ድምፅ ፡ ልቡን ፡ የማይቀሰቅሰው ፡ ሰው ፡ ክሕደት ፡ ተንኰልና ፡ ቀማኛነት ፡ አያጣም ። የነፍሱ ፡ ሕዋሳቶች ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፤ ( ጨለማ ፡ ) የቀፈፉ ፡ ፍቅሩም ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ የጠቈረ ፡ ነው ። ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ተጠንቀቁ ። »



በጥንት ፡ ዘመን ፡ እንኳ ፡ በሺና ፡ አገር ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ አስቀድሞ ፡ የተወለደው ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ፈላስፋ ፡ ኮንፉሲዩስ ፤ ሙዚቃ ፡ በጣም ፡ ይወድ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ላንዱ ፡ ተማሪው ፡ ሲነግረው ፡ « አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ትልቅ ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ብትፈልግ ፡ ሙዚቃውን ፡ ስማ ። » አለው ፡ ይባላል ።

ቅኔ ፡ ከጥንት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የተወደደና ፡ የተከበረ ፡ ነው ። አልሲቢያድ ፡ የሚባለው ፡ የሶቅራጥስ ፡ ተማሪ ፤ የግሪክ ፡ ጄኔራል ፤ በልጅነቱ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡ መምህሩን ፡ የሆሜርን ፡ ቅኔ ፡ ስጠኝ ፡ አለው ። መምህሩ ፡ ግን ፡ ሆሜርን ፡ በጭራሽ ፡ ስለማያውቀውና ፡ ቅኔውንም ፡ ስላላነበበ ፡ ሆሜር ፡ ማለት ፡ ማነው ፡ ? ብሎ ፡ መለሰለት ። አልሲቢያድ ፡ ሆሜርን ፡ የማያውቅ ፡ መምህር ፡ በማግኘቱ ፡ ተናዶ ፡ በጥፊ ፡ መታው ፡ ይባላል ።

ሕዝብ ፡ ከትልቅ ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ሲደርስ ፡ ታላላቅ ፡ ባለቅኔዎች ፡ ያገኛል ። በመሠልጠናቸው ፡ ግሪኮች ፡ ሆሜርንና ፡ ኤሺልን ፤ ሮማውያን ፡ ቬርጊልንና ፡ ሆራስን ፡ እንግሊዞች ፡ ሻኬስፒርና ፡ ሚልተንን ፤ ፈረንሳይዎች ፡ ኮርኔይና ፡ ራሲንን ፡ ጀርመኖች ፡ ጎትና ፡ ሺለርን ፤ መስኮቦች ፡ ፑሽኪንን ፡ አፈሩ ።

ቀዳማዊ ፡ ናፖሌዎን ፡ ቅኔን ፡ አፍቃሪ ፡ በመሆኑ ፡ ትልቁ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ባለቅኔ ፡ ኮርኔይ ፡ የተፈጠረው ፡ በኔ ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የመስፍን ፡ ማዕርግ ፡ እሰጠው ፡ ነበር ፡ አለ ፡ ይባላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ አብዛኞች ፡ ሰዎች ፡ የጥበብ ፡ ዋጋ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ስለማያውቁት ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መናቅና ፡ መረሳት ፡ እየደረሰባቸው ፡ ዓለምን ፡ ድንቁርና ፡ ሲያጠቃት ፡ ይኖራል ።

ኒውተን ፡ ሁልጊዜ ፡ አሳቡ ፡ ጥበብን ፡ በመመርመር ፡ ተጠምዶ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ስለነበረ ፡ ለጨዋታና ፡ ለጊልታ ፡ ጊዜ ፡ አልነበረውም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሕይወቱን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ሲናገሩ ፡ ኒውተን ፡ አለ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በቀር ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሲስቅ ፡ ታይቶ ፡ አይታወቅም ። ይኸውም ፡ ጅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የኦክሊድ ፡ ትምህርት ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

ጋሊሌዎ ፡ ዓይነ ፡ ስውር ፡ ሆኖ ፡ በችግር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የሞተው ። «የኢየሩሳሌም ፡ ነፃ ፡ መውጣት ፡» የተባለውን ፡ ቅኔ ፡ የጻፈ ፡ ታሶ ፤ የጥንቶቹን ፡ የቅኔ ፡ ድርሰቶች ፡ ሊወዳደር ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ሙያውን ፡ የሚያውቅለት ፡ ሰው ፡ ባለማግኘቱ ፡ በችግርና ፡ በብስጭት ፡ በወህኒ ፡ በመታሰርና ፡ በመፈታት ፤ በመሰደድ ፤ በመራብ ፤ ዕድሜውን ፡ ፈጀው ።

በመጨረሻ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ክሌሜንት ፡ ስምንተኛ ፡ ዋጋውን ፡ መስክረውለት ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ሊያገኝ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሲጠሩት ፡ በጭንቁና ፡ በመከራው ፡ ሰዓት ፡ አልመጣም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ ያለው ፡ ሞት ፡ አጣድፎ ፡ ክብሩን ፡ የመቀበያ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሰጥ ፡ የዋዜማው ፡ ዕለት ፡ ሞተ ።

ሰማዕትነት ፡ የሞላበት ፡ የስንቱ ፡ ሊቅ ፡ ታሪክ ፡ ተጠርቶ ያልቃል ። ሚኬላንጄሎ ፤ ቤቶቨን ፤ ሌዎፓርዲ ፤ ጉኖድ ፤ ሹማን ፤ ኒች ፤ ሄን ፤ እነዚህ ፡ አብዶው ፡ ወይም ፡ ደዌ ፡ አድሮባቸው ፡ ነው ፡ የሞቱት ። ዶስቶዬቭስኪ ፡ ሕይወቱን ፡ ሙሉ ፡ የኖረው ፡ በሕመምና ፡ በችግር ፡ በግዞትና ፡ በመከራ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ጥበብን ፡ ለመመርመር ፡ ዕድሜያቸውን ፡ በመከራና ፡ በችግር ፡ ያሳለፉ ፡ ሊቃውንት ፡ ቁጥራቸው ፡ ብዙ ፡ ነው ። የሚበልጡት ፡ ታላላቆች ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ፡ ሕይወታቸው ፡ በመከራ ፡ ነው ፡ ያለፈችው ።

ሶቅራጥስ ፡ ጠላቶች ፡ ተነሥተውበት ፡ ስለተከሰሰ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደውበት ፡ መርዝ ፡ ጠጥቶ ፡ እንዲሞት ፡ ታዘዘ ። በእሥር ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ ወዳጆቹ ፡ ሸሽቶ ፡ እንዲያመልጥ ፡ ርዳታቸውን ፡ ሊያደርጉለት ፡ ተዘጋጅተው ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሶቅራጥስ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተፈረደብኝ ፡ በግፍ ፡ ቢሆን ፡ ያገሬን ፡ ሕግ ፡ ማክበር ፡ ግዴታ ፡ አለብኝ ፡ በማለት ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ መልካም ፡ አብነት ፡ ለመሆን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሰዓት ፡ ፍልስፍናን ፡ እያስተማረ ፡ የተፈረደበትን ፡ መርዝ ፡ ጠጥቶ ፡ ሞተ ።

ያሜሪካን ፡ አገር ፡ ያገኘ ፡ ክስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ ምቀኞች ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተውበት ፡ ከእስፓኛ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ አጣልተውት ፡ ታሰረ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ ቢገለጥና ፡ ንጽሕናው ፡ ቢታወቅ ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍርድ ፡ ሳያገኝ ፡ ስለሞተ ፡ የታሰረበት ፡ ሰንሰለት ፡ አብሮ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እንዲቀበር ፡ ለምኖ ፡ አረፈ ።



ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ በምስልና ፡ በሥዕል ፡ ያስጌጠ ፡ ሚኬላንጄሎ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ምስል ፡ በመቅረጽና ፡ ሥዕል ፡ በመሳል ፡ ሙያ ፡ ተወዳዳሪና ፡ መሰል ፡ የሌለው ፡ ነው ። እሱም ፡ ቁመቱ ፡ አጭር ፡ ወገቡ ፡ ጉባጣ ፡ ነበር ። ሚኬላንጄሎ ፡ ገንዘብ ፡ የማይፈልግ ፤ ክብርን ፡ የማይሻ ፤ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ እንደ ፡ ባሕታዊ ፡ ንብረት ፡ ሳይዝና ፡ ሚስት ፡ ሳያገባ ፡ ጥበብን ፡ ብቻ ፡ በመውደድ ፡ ዕድሜውን ፡ ፈጀ ።

ሞዛር ፡ ያደገው ፡ የጀርመን ፡ ንግሥት ፡ በነበረችው ፡ በማርያ ፡ ቴሬዛ ፡ ቤት ፡ መንግሥት ፡ ነው ። እሷም ፡ ባገራችን ፡ በሚገኘው ፡ የማሪያ ፡ ቴሬዛ ፡ ብር ፡ በሚባለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ መልኳ ፡ የሚታየው ፡ ናት ። ጥበብ ፡የምትወድ ፡ ደግና ፡ ብልህ ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ደሆች ፡ ልጆች ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቷ ፡ እየወሰደች ፡ ጡቷን ፡ እያጠባች ፡ ታሳድግ ፡ ነበር ይባላል ። እሷ ፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፤ «(ጥቁር) የኀዘን ፡ ቀለም ፡ ባውሮፓ ፡ ካርታ ፡ ላይ፡ ፈሰሰበት ፡» ብሎ ፡ ተናገረ ።

ሞዛር ፡ ገና ፡ በሕፃንነት ፡ በስምንት ፡ ዓመቱ ፡ ፒያኖ ፡ ሲጫወት ፡ ለትንግርት ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ንግሥቲቱም ፡ የሞዛርን ፡ ሙዚቃ ፡ ስሰማ ፡ ሰው ፡ መሆኔን ፡ እረሳዋለሁ ፡ ትል ፡ ነበር ። በጣም ፡ ስለምትወደው ፡ በቀልድም ፡ ይሁን ፡ በውነት ፡ ልጁዋን ፡ ልዕልት ፡ ማሪያ ፡ አንቷኔትን ፡ እድርልሃለሁ ፡ ትለው ፡ ነበር ። ሞዛር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ደሀ ፡ ነኝ ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ልዕልት ፡ ናት ፡ ይህ ፡ እንደምን ፡ ይሆናል ? ሲል ፡ አንተም ፡ የሙዚቃ ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ፡ ብላ ፡ ትመልስለት ፡ ነበር ።

ይሁን ፡እንጂ ፡ ሞዛር ፡ በኋላ ፡ ደኃ ፡ ንግሥት ፡ ሞታ ፤ ማሪያ ፡ አንቷኔትም ፡ የፈረንሳዊን ፡ ንጉሥ ፡ ሉዊ ፡ አሥራ ፡ ስድስተኛን ፡ አግብታ ፡ የፈረሳንይ ፡ ሕዝብ ፡ሬቮሊሲዮን ፡ ባነሣ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ተገደለች ። ሞዛርም ፡ በድህነት ፡ ኖረና ፡ የሳል ፡ በሽታ ፡ ይዞት ፡ በሠ

ላሳ ፡ ስድስት ፡ ዓመቱ ፡ ሞተ ። ከመሞቱም ፡ በፊት ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የተሰወረ ፡ ማን ፡ መሆኑ ፡ የማይታወቅ ፡ ሰው ፡ አጠገቡ ፡ ቀርቦ ፡ ለፍታትህ ፡ እንዲሆን ፡ «ሬኩዬም ፡ »የሚባለውን ፡ የኀዘን ፡ ዜማ ፡ እንድትጽፍ ፡ ብሎት ፡ አዘዘውና ፡ ሄደ ።

ሾፐን ፡ የሚባለውም ፡ ዕድሚውን ፡ የፈጀው ፡ በድህነት ፡ ነው ። ልብሱ ፡ መናኛ ፤ ጤንነቱ ፡ የተበላሸ ፡ በሽተኛ ፤ አኗኗሩ ፡ ሁልጊዜ ፡ በችግር ፡ ነበር ። ከጌትነትም ፡ ይልቅ ፡ ድኀነትን ፡ ይወድ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዕውቀቱን ፡ እያደነቁ ፡ በገንዘብ ፡ ሊረዱት ፡ ሲፈልጉ ፡ ሙዚቃ ፡ ከሰማይ ፡ የተገኘች ፡ ጸጋ ፡ ስለሆነች ፡ በምድራዊ ፡ ገንዘብ ፡ ልትለወጥና ፡ ልትገመት ፡ አይገባትም ፡ እያለ ፡ አይቀበላቸውም ፡ ነበር ።

ሁልጊዜ ፡ የሚያስበው ፡ ጥበብንና ፡ ሞቱን ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ዘለዓለም ፡ ከትካዜ ፡ አልወጣም ። አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ «ሾፐን ፡ ዕድሚውን ፡ ሙሉ ፡ ሞቶ ፡ የኖረ ፡ ሰው ፡ ነው ። » ይለዋል ።

ቤቶቨንም ፡ እንደዚሁ ፡ ሕይወቱን ፡ የፈጀው ፡ በችግርና ፡ በሀብስጭት ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ግማሽ ፡ ዕድሜውን ፡ ጆሮው ፡ ደንቆሮ ፡ አልሰማ ፡ ስላለው ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ ኀዘን ፡ አልተለየውም ። ከብስጭቱ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ለመግደል ፡ እስከ ፡ ማሰብ ፡ ደርሷል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሙያው ፡ ይበልጥ ፡ ገነነ ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ አልደከመም ።

ቤቶቨንም ፡ እንደ ፡ ሞዛር ፡ ትልቅ ፡ ስጦታ ፡ ነበረው ። ሙዚቃ ፡ ሲቀኝም ፡ ከሰማይ ፡ ድምፅ ፡ የሚያቀብለው ፡ መንፈስ ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያን ፡ የመሰለውን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ፍርሃትና ፡ ሽብር ፡ እየነዛ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አሳብን ፡ በትካዜ ፡ እየጨበጠና ፡ እየዋጠ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ እያነሣ ፤ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ ስም ፡ በሌለው ፡ ስሜት ፡ የሰውን ፡ አእምሮ ፡ እየበጠበጠ ፡ የሚጫወትበትንና ፡ ሲሠራ ፡ ሲያፈርሰው ፡ የሚውልበትን ፡ ድምፅ ፡ ከወዴት ፡



እንደሚያፈልቀው ፡ ለማወቅ ፡ የማይቻል ፡ ትልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። አንድ ፡ ሙዚቀኛ ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ የቤቶቨን ፡ ሙዚቃ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትና ፡ ገሃነም ፡ ለቅሶና ፡ እልልታ ፡ ሕይወትና ፡ ሞት ፡ ሆኖ ፡ እየመጣ ፡ ይህን ፡ የማይገናኝና ፡ የማይስማማ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተፈራራሽ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በሚያስደንቅ ፡ ጥበብ ፡ እያዛመደ ፡ አዋሕዶ ፡ ውበትና ፡ ግርማ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻልበትን ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተቀበለ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ቤቶቨን ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ይላል ። «ሙዚቃ ፡ የነፍሲ ፡ አየር ፡ ነች ። » ይል ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ቤቶቨን ፡ መልኩ ፡ የማያምር ፤ ልብሱ ፡ ሁልጊዜ ፡ አሮጌ ፤ ኑሮው ፡ የተጐሳቆለ ፡ ዘላለም ፡ ችግረኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ቤቶቨን ፡ በኑሮው ፡ በጣም ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ ነበረበት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጫማዎቹ ፡ አለቁበትና ፡ ያለ ፡ ውዱታው ፡ ከቤቱ ፡ ሳይወጣ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሰነበተ ። ወዳጁ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘውና ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ ሰሞን ፡ አላየሁህም ፡ አሞህ ፡ ኖርዋል ፡ ወይ ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ቤቶቨንም ፡ እኔስ ፡ ደኅና ፡ ነኝ ፡ የታመሙት ፡ ጫማዎቼ ፡ ነበሩ ፡ ብሎ ፡ በመቀለድ ፡ መለሰለት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሙያውን ፡ ራሱ ፡ ገምቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ብዙ ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ለመተው ፡ ከመሥራት ፡ አልቦዘነም ። ለምሳሌ ፡ ቤቶቨን ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ። «ገትና ፡ እኔ ፡ ቂሻሻ ፡ የሆነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማይነካው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ያለን ፡ ሰዎች ፡ ነን ። እንደ ፡ እኛ ፡ ያሉ ፡ ሁለት ፡ ታላላቆች ፡ ሰዎች ፡ ባለንበት ፡ ቦታ ፡ ሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ የኛ ፡ ትልቅነት ፡ ሊሰማቸው ፡ ይገባል ። ገትና ፡ እኔ ፡ ላገራችን ፡ ለጀርመን ፡ ክብርዋ ፡ ነን ። »

ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ የመጀመሪያ ፡ እርምጃዋን ፡ በምታደርግበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ የመሰለ ፡ ጥቅሙን ፡ በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከልብና ፡ ከተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ በፈለቀ ፡ ስሜት ፡ ጥበብን ፡ የሚወዱ ፡ ንጉሥ ፡ በማግኘቷ ፡ የታደለች ፡ ነች ። የዕውቀት ፡ ጥቅም ፡ የማይገባውና ፡ የጥበብ ፡ ፍቅር ፡ ያላደረበት ፡ ንጉሥ ፡ ሲነግሥ ፡ ላገር ፡ ትልቅ ፡ ጉዳት ፡ መሆኑን ፡ በሌላ ፡ ዘንድ ፡ ሳይሆን ፡ በሠለጠኑት ፡ በአውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ማስረጃ ፡ እናገኛለን ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሙሉ ፡ የዕውቀት ፡ ሙያ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለማፍራት ፡ ከምትችልበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ገና ፡ ባትደርስ ፡ በዘመናቸው ፡ ለተገኙት ፡ ሰዎች ፡ ባደረጉት ፡ ርዳታ ፡ ጥበብን ፡ ደጋፊ ፡ ለመሆናቸው ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ብዙ ፡ ማስረጃ ፡ ሰጥተዋል ። አሁን ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ ባዪ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ የዕውቀት ፡ ጥቅም ፡ ባለመታወቁ ፡ በትምህርቱ ፡ ከሚኒስትርነት ፡ ማዕርግ ፡ የደረሰ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አልነበረም ። ባዪ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመን ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ዋጋቸውን ፡ እንዳገኙ ፡ የተገለጠ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ይህንን ፡ መናገር ፡ የሚያስፈልግ ፡ አይደለም ። ብቻ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ትልቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ደራሲ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘንድ ፡ ያገኙት ፡ ክብርና ፡ ማዕርግ ፡ ትልቁ ፡ የጀርመን ፡ ሊቅ ፡ ፈላስፋና ፡ ባለቅኔ ፡ የሆነው ፡ ገት ፤ ሻርል ፡ አጉስት ፡ በተባለው ፡ የቬማር ፡ መስፍን ፡ ዘንድ ፡ አግኝቶት እንደነበረው ፡ የመሰለ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የክብር ፡ ዋጋ ፡ መሆኑን ፡ ማሳሰብ ፡ ይበቃናል ። በዚህም ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የዕውቀት ፡ ደጋፊዎችና ፡ የጥበብ ፡ ወዳጆች ፡ የሆኑ ፡ ነገሥታት ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፡ የተቀበሉትን ፡ ክብር ፡ ይካፈላሉ ።

ደራስያንን ፤ ሥዕል ፡ ሣሊዎችን ፤ ሌሎችንም ፡ ማነኛውም ፡ ዓይነት ፡ የጥበብ ፡ ሙያ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መርዳትና ፡ ማበረታታት ፡ የዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ ስለሆነና ፡ ይህንኑም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚያውቀው ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ ንጉሣዊ ፡ ችሮታ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በዝርዝር ፡ ልንጠራቸው ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።



## መደምደሚያ ፤

ይህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመምራት ፡ ያላቸው ፡ ትጋትና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባይ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶችም ፡ የሚያሳዩት ፡ የትምህርት ፡ ፍቅር ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ እንዲያገኝ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰላምን ፡ ልታገኝ ፡ ያስፈልጋታል ።

ኢጣሊያ ፡ ኤርትራን ፡ ከያዘች ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰላምን ፡ አላገኘችም ። ይልቁንም ፡ አሁን ፡ በመጨረሻው ፡ ጦርነት ፡ ኢጣሊያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በያዘችበት ፡ ጊዜ ፡ የተማሩትን ፡ ወጣቶቿን ፡ ስለፈጀቻቸው ፡ ዋና ፡ አሳቧ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በድንቁርና ፡ ጨቁና ፡ ለማኖር ፡ መሆኑን ፡ ሥራዋ ፡ መስክሮዋል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ በማወቃቸውና ፡ ባውሮፓ ፡ ተምረው ፡ በማደጋቸው ፡ ይኸው ፡ ከኃጢአት ፡ ተቆጥሮባቸው ፡ በጥይት ፡ የተደበደቡ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቍጥራቸው ፡ ብዙ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በዚሁ ፡ በኢጣሊያ ፡ ይዞታ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ትምህርት ፡ ጨርሰው ፡ መከልከላቸውና ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ትእዛዝ ፡ መዘጋታቸው ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ። ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ቀርቶ ፡ በቤቱ ፡ ውሥጥ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ማለት ፡ በእንግሊዝ ፡ ወይም ፡ በፈረንሣይ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍት ፡ የተገኘበት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰው ፡ በኢጣሊያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ፍርድ ፡ የሚያደርስ ፡ ኃጢአት ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠርበት ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ ኢጣሊያ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አሳብ ፡ የምትመራ ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ኤርትራና ፡ ወደ ፡ ሱማሌ ፡ ግዛቶቿ ፡ እንድትመለስ ፡ ያለም ፡ መንግሥታት ፡ ጉባዔ ፡ ቢፈቅድላት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሦስተኛውን ፡ ጦርነት ፡ እንድታነሣ ፡ የምትዘጋጅበትን ፡ መንገድ ፡ መክፈትና ፡ ኢትዮጵያም ምዕራባዊን ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዳታገኝ ፡ ተቀናቃኝ ፡ የሆነቻት ፡ ምቀኛ ፡ ጠላቷ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዳትራመድ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ተንኮል ፡ መሰናክል ፡ የምትሆንበትን ፡ ዘዴ ፡ መፍጠር ፡ ይሆንበታል ።

